

የኢትዮጵያ መለኮታዊ ዙፋን።
ቅዱሳን መላእክት የሚጠብቁት፡ የኢየሱስ ክርስቶስና የድንግል ማርያም መንበረ መንግሥት።
(ሐተታው፡ በገጽ ፩፻፰-፩፻፲፩ እና ፪፻፷፫-፪፻፷፮ ይገኛል።)

# ኢትዮጵያ፡
# የዓለሙ መፍረጃ!

**ለ፯ሺ፬፻፺፫ ዓመታት በቆየው ዕድሜዋ፡
ታላላቅ መከራዎችን ያሳለፈች፥ በዓለም ላይ
ለደረሰውና ለሚደርሰው መለኮታዊ ኵነኔ፡
መፍረጃ፥ ለቅዱሱ ኪዳን ባለአደራም የኾነች
የእግዚአብሔር ሕዝብ አገር!**

---

***ፍጥረተ ዓለሙን ሊቀጣ ተቃጥቶ ካለው፡
ከመጪው ታላቅ መቅሠፍታዊ ሠይፍ፡
ለመዳን ይችል ዘንድ፡ ይህ፡ የአሁኑ የሰው ልጅ
ትውልድ፡ ዛሬ እንደገና የቀረበለትን፡
ይህን አምላካዊ የማስጠንቀቂያ መልእክት ሰምቶ፡
ከጥፋቱ ይመለስ ይኾን?***

---

**የመልእክቱ አቅራቢ
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደኢየሱስ፡፡**
**(ገጽ ፩፻፺፪-፩፻፺፫ ይመልከቱ)**

ኢትዮጵያ፡

የደራሲው ባለመብትነት፡ በሕግ የተጠበቀ ነው።

፲፱፻፺፫ ዓመተ ምሕረት።
Copyright © 2001 Ermias Kebede Wolde-Yesus

ይህን መልእክታዊና ትምህርታዊ መጽሐፍ፥ ደግሞም፡ "ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ!" እና Ethiopia: The Classic Case የተባሉትን፥ ሌሎችንም፡ ወደፊት እየታተሙ የሚወጡትን መጻሕፍት ለማግኘት፡ ከዚህ በታች በተመለከቱት፡ ባሳታሚው አድራሻዎችና የመገናኛ መስመሮች፡ መጠየቅና መጠቀም ይቻላል።

---

አሳታሚ
Publisher
ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት።
**Ethiopia: The Kingdom of God Services**
መልእክት ሣጥን ቁጥር ፰፻፲፪ P. O. Box 812
ስልክ ቁጥር ፲፮-፲፰-፹፭ እና ፳-00-፹፭ Tel. Nos. 16-18-85 & 20-00-85
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ። Addis Abeba, ETHIOPIA
ወይም or
**P. O. Box 43262 ~ Washington, DC 20010-9262 ~ USA.**
**Phone: 301-587-8074 ~ Fax: 301-587-1971**
Email: ekogyesus@aol.com
Web Site: www.ethiopiakingdomofgodserv.org

+ አአትብ ገጽየ ወኵለንታየ፡ በትእምርተ መስቀል +

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፥ አሐዱ አምላክ፤

በስመ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ አንበሳ መዋዒ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ፥ ሥርወ ለዳዊት፥ ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ፥ ንጉሠ ጽዮን ወንጉሠ ነገሥት ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ፤

በስመ እግዝእትነ ወእምነ ወመቅደስነ ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፥ እንተ ይእቲ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ፡ ዘታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር፡ በእንተ ኵሉ ዓለም፥ ንግሥተ ጽዮን ወንግሥተ ነገሥት ወንግሥታት ዘኢትዮጵያ፤

አነ፡ ላእከ ኢትዮጵያ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፥

አብጻሕኩ ለክሙ ዛተ መልእክተ!

አሜን::

<u>ትርጉም</u>

+ በመስቀል ምልክት፡ ፊቴንና ኹለንተናዬን አማትቤ +

አንድ አምላክ በኾነ፡ በአብ፥ በወልድ፥ በመንፈስ ቅዱስ ስም፡

የጽዮን ንጉሥ፥ የኢትዮጵያ ንጉሦችና ንግሥቶች ንጉሥ፥ በመልከ ጼዴቅ ሹመት፡ የዘለዓለም ካህን በኾነው፥ ከዳዊት ግንድ፥ ከይሁዳ ነገድም፡ በአሸናፊ አንበሳነት በወጣው፡ በጌታችን፥ በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፤

የጽዮን ንግሥት፥ የኢትዮጵያ ንጉሦችና ንግሥቶች ንግሥት በኾነችው፥ አምላክን በወለደች፡ ይህችውም፡ አገራችን ኢትዮጵያ ኾና፡ ስለዓለሙ ኹሉ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር በዘረጋችው፡ በእመቤታችን፥ እናታችንና መቅደሳችን ድንግል ማርያም ስም፤

እኔ፡ የኢትዮጵያ አገልጋይ፡ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ ኢየሱስ፥

ይህችን መልእክት አምጥቼላችኋለሁ!

አሜን::

## የምስጋና መታሰቢያ

ቸርና ኃያል የኾነው እግዚአብሔር አምላክ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን ከመሠረተበት፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ እስከዛሬ ድረስ፡ በምድር ላይ፡ በሰዎች መካከል የተገኙትን እውነተኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ጨርሰው ከመጥፋት እየታደጋቸው፡ ኢትዮጵያ፡ በመለኮታዊው ማንነቷ፡ ህልውናዋን እንድትቀጥል ስላደረገ፥

ይህና ያለፉት የመልእክት ድርሰቶቼ፡ በዚህ መልክ ታትመው እስኪወጡ፥ ተሠራጭተውም፡ ከአንባቢ ዘንድ እስኪደርሱ፡ ባለው ከባድ ውጣ ውረድ፡ ከጽንሰ ሐሳቡ ጀምሮ፡ በትችትና በምክር፥ በገንዘብና በጉልበት፡ በሙሉ ዓቅማቸው በመሳተፍ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾኑችው፡ ለኢትዮጵያ፡ በምናበረክተው፡ በነፍሳዊው፥ በሥጋዊውና በመንፈሳዊው የቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖታችን ሕይወትና አገልግሎት ያልተለዩኝን፡ ኪዳናዊት ባለቤቴን ወ/ሮ ራሔል ዘካርያስን፥ ኪዳናውያት ልጆቻችንንና ኪዳናውያን ባለቤቶቻቸውን፡ ወ/ሪት መልእክተ ኤርምያስን፥ ሐኪም ትምህርተ ኤርምያስንና መሐንዲስ ዳንኤል ገላንን፥ ወ/ሪት ስብከተ ኤርምያስን፥ ወ/ሮ ሃይማኖተ ኤርምያስንና አቶ ኀሩየ ሥላሴ ምትኩን፥ እንዲሁም፡ ኪዳናዊዉን ልጅ ሰማዕተ ኤርምያስን ስለሰጠኝ፥

ከእነርሱም ጋር፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት የገድል ባልደረቦችን፡ ለዚህ አገልግሎት ጠርቶ ስላሰባሰበ፥

በዚህ ተልእኳችን ምክንያት፡ እያንዳንዳችን በግል፥ በአጠቃላይም በጋራ፡ ከያግጣሚው የሚደርስብንን ፈተናና መከራ፡ እንድንቋቋመው እያስቻለን፥ ከክፉውም ኹሉ እየጠበቀን፡ በዚሁ የገድል ግዳጃችን ጽንተን እንገኝ ዘንድ፡ በረድኤቱ ስላልተለየን፡ አመሰግነዋለሁ።

ለዚህ፡ የምስጋና ቁርባን፡ ይህ መጽሐፍ፡ የዘለዓለም መታሰቢያ ኾኖ ይኖራል።

የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ፡ ከ፲፱፻፷፯ እስከ ፲፱፻፹፭ ዓ. ም. ባሳለፈው የፈተናና የመከራ ዘመን፡ ደርግ፡ አዲስ አበባ፡ በታላቁ ቤተ መንግሥት ግቢ፡ አቋቁሞት በነበረው ወህኒ ቤት፡ በእሥራት፥ ከዚያ፡ በአገሩ በኢትዮጵያ፡ በግዞት፥ በመጨረሻ፡ በአሜሪካ ምድር፡ በስደት ሣለ፡ ከጻፋቸው ድርሰቶቹ መካከል፡ Ethiopia: The Classic Case በሚል ርእስ፡ በዚያው በባዕድ አገር፡ አሳትሞ፡ ለሕዝባዊ ንባብ ካበቃው ዕትምና በማከታተል፡ በአገራችን ታትሞ ከተሠራጨው፡ "*ኢትዮጵያዊው፥ በማንነቱ ፍለጋ*" ከተባለው፡ የመጀመሪያ ጥራዝ ቀጥሎ፡ ይህ መጽሐፍ፡ በዚያ፡ በእንግሊዝኛው ዝግጅት ውስጥ ከተገለጸው በላይ፡ በሰፊው ታክሎበት፡ በተለይ፡ ለኢትዮጵያውያን፡ በነሐሴ ፲፯ ቀን፥ ፲፱፻፺፫ ዓ. ም. አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ፡ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ።

ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ
ኢየሱስ ክርስቶስ
ካህኑ ለዓለም፡ ንጉሠ ጽዮን
<u>ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u>

The Conquering Lion of The Tribe of Judah
Jesus Christ
Eternal Priest, King of Zion,
King of Kings of Ethiopia

ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር
ድንግል ማርያም
እሙ ወእምነ፡ ንግሥተ ጽዮን
<u>ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u>

Ethiopia Stretches out Her Hands to God
The Virgin Mary
Mother of God and Our Holy Mother
Queen of Zion and Ethiopia



## በመጽሐፉ ተቀዳሚ ገጽ ላይ የሠፈረው፡ የመለኮታዊው መንግሥት ምልክትና ማኅተም

## <u>መግለጫ</u>


በኅብረ ቀለማት የተከናወነው፡ ይህ ቅዱስ ዓርማ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ለኾነችው ኢትዮጵያ፡ መለኮታዊ ምልክቷና ታላቁ ማኅተሟ ነው።

፩ኛ፡- በላይኛው ወገን ያለው፡ የአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ ቀለማትን የያዘው ሥዕላዊ ክበብ፡ ኖኅ፡ በቀስተ ደመና ምልክትነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ቃል ኪዳን የሚያመለክተው፡ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ሲኾን፡ የሰንደቅ ዓላማውን፡ የአንድነቱንና የሦስትነቱን ምሥጢር፡ ከብዙው በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፡- ሀ) የአብ፥ የወልድ፥ የመንፈስ ቅዱስን፡ አንድ አምላክነት፥ ለ) የነፍስ፥ የሥጋንና የመንፈስን፡ አንድ ሰውነት፥ ሐ) የኢትዮጵያዊን አንድ የውህደት ዘር፡ ሴማዊነት፥ ካማዊነትና ያፌታዊነት፥ መ) የኢትዮጵያን መለኮታዊ መንግሥት፡ ሕዝባዊነት፥ ክህነታዊነትና መለካዊነት ያስረዳል።[፩]

፪ኛ፡- በመካከለኛው ወገን ያለው ሥዕላዊ ሰውነት፡ ኢትዮጵያ፡ እጆቿን ወደእግዚአብሔር እንደዘረጋች የሚያሳይ ሲኾን፡ ይህችው እመቤት፡ የአምላክ እናት፥ የጽዮንና የብሔረ ኢትዮጵያ፥ የፍጥረተ ዓለሙም ንግሥት የኾነችው፡ ድንግል ማርያም መኾኗን ያመለክታል።[፪]

፫ኛ፡- በታችኛው ወገን ያለው ሥዕላዊ አካል፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ተብሎ፡ በእግዚአብሔር ቃል የተነገረለትን፡ ዘለዓለማዊዉን ካህንና የጽዮንን ንጉሥ፥ የብሔረ ኢትዮጵያና የፍጥረተ ዓለሙም ንጉሠ ነገሥት የኾነውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያሳያል።[፫]

ኢትዮጵያ:



የድንግል ማርያምና የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌና ጥላ በመኾን: በቅድሚያ ታይተው በነበሩት:
በኢትዮጵያዊቷ ንግሥት ማክዳና በእስራኤላዊው ንጉሥ ሰሎሞን የዘር ውህደት:
የኢትዮጵያን መለኮታዊ ዙፋን: ለመጨረሻዎቹ ባለቤቶች ያዘጋጀው: ኪዳነ ዳዊት::
(ሓተታው: በገጽ ፩፻፭-፩፻፲፩ ይገኛል::)

# ኢትዮጵያ፡

“ንግሥተ ዓዜብ (ኢትዮጵያ)፡ በፍርድ ቀን ተነሥታ፡ ከዚች ትውልድ ጋር ትፋረዳለች፤ ታሳፍራታለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ፡ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ÷ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ![፬]

“ከዚህ በኋላ፡ ሌላ ታላቅ መልአክ፡ ደመናን ተጐናጽፎ፡ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበር። ፊቱ፡ እንደፀሓይ÷ እግሮቹም፡ እንደእሳት ዓምዶች ነበሩ። በእጁም፡ የተገለጠች መጽሐፍን ይዟል። በቀኝ እግሩ፡ በባሕር ላይ ቆመ፤ በግራ እግሩም፡ በምድር ላይ ተረገጠ። እንደሚያገሣ አንበሳም፡ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ በጮኸም ጊዜ፡ ይጻፍ ዘንድ ስላለው ነገር፡ ሰባቱ ነጐድጓድ፡ በየቃላቸው ተናገሩ። .......

“ያ፡ ከሰማይ የሰማሁት ቃል፡ ዳግመኛ እንዲህ ሲል ተናገረኝ፡ "ኺድና፡ ያችን የተገለጠችውን መጽሐፍ፡ በባሕርና በየብስ ላይ ቆሞ ካለው፡ ከዚያ መልአክ እጅ ተቀበላት!" “እኔም፡ ወደዚያ መልአክ ሄጄ፡ ያችን መጽሐፍ፡ "ስጠኝ!" አልኩት።

“እርሱም፡ "ውሰድና ብላት! ሆድህንም ትምረራት! ለአፍህ ግን፡ እንደማር የምትጣፍጥ ትኾን!" አለኝ።

ያችን መጽሐፍ፡ ከመልአኩ እጅ ተቀብዬ፡ በላኋት፤ ለአፌ የምትጣፍጥ ኾነችኝ፤ በዋጥኋት ጊዜ ግን፡ ለሆዴ መራራ ኾነች።

“ዳግመኛም፡ "ለሕዝብና ለአሕዛብ÷ ለአህጉርና ለብዙ ነገሥታት፡ እንደገና ታስተምር ዘንድ አለህ፤" አለኝ።”[፭]

# የእግዚአብሔር እውነት፡

## ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት፡
## የምትሰጠው ምስክርነት፡

እና

## በእርሷ ላይ በሥውር የተፈጸመው ክህደት፡
## በቅርቡ የተረከሰው መለኮታዊ እሳት፡
## ያቀጣጠለው አስደንጋጭ መቅሠፍት!

ኢትዮጵያ፡




ኢትዮጵያ፡ ከተወዳጅ ልጅዋ ጋር።
(ሐተታው፡ በገጽ ፯፥ ፳፭-፳፫፥ ፩፻፯-፩፻፱፥ ፩፻፷፭፥ ፩፻፹፯፥ ፩፻፹፱፥ ፩፻፺፩፥ ፫፻፲ ይገኛል።)

# ማ ው ጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ (የውስጥ ሽፋን ከነማሳሰቢያው)፤ | ፩ |
| የኅትመት መምሪያና አድራሻ፤ | ፪ |
| የመግቢያ ጸሎት፤ | ፫ |
| የምስጋና መታሰቢያ፤ | ፬ |
| የመለኮታዊው መንግሥት ማኅተም፥ ከነቃለ አጼው ርእስ፤ | ፭ |
| " " " " " መግለጫ፤ | ፮ |
| " " " " " ጥቅሶች፤ | ፯ |
| **የእግዚአብሔር እውነት፡ ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት የምትሰጠው ምስክርነት፤ በእርሷም ላይ በሥውር የተፈጸመው ክህደት፡ በቅርቡ የተረኰሰው መለኮታዊ እሳት፥ ያቀጣጠለው አስደንጋጭ መቅሠፍት፤** | ፱ |
| ማውጫ፤ | ፲፩ |
| መቅድም፡ የዚህ መልእክት አጠቃላይ ዓላማ፤ | ፳፩ |
| በተለይ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች፤ | ፳፬ |
| የፈላስፋው ገዘከሬ ነገር፤ | ፴፪ |
| የ"እብደት" ትርጉም፡ እንደተመልካቹ አቋም ነው፤ | ፴፭ |
| ስለአንባቢው ብቅዓት፤ | ፴፯ |
| የመቅድሙ ማጠቃለያ፤ | ፵ |


## ክፍል አንድ


| | |
|---|---|
| ***የእግዚአብሔር እውነት፡ ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት፡ የምትሰጠው ምስክርነት፡፡*** | ፵፫ |
| **ምዕራፍ ፩** | |
| **ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያዊው እና ኢትዮጵያዊነት፡፡** | ፵፭ |
| ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ ከየት ተገኘ? | ፵፮ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለዐምሓራነት ስትፋረድ! | ፵፮ |
| የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መገለጫዋ ሰውነት፤ | ፶፩ |
| **ምዕራፍ ፪** | |
| **ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፡፡** | ፶፬ |
| የመጀመሪያው ቃል ኪዳን፡- ኪዳነ አዳም ወሔዋን፤ | ፶፭ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለጋብቻ ሥርዓቷ ስትፋረድ! | ፶፯ |
| የጋብቻ አለመከበር ጠንቅ፤ | ፷ |
| ኹለተኛው ቃል ኪዳን፡- ኪዳነ ኖኅ፤ | ፷፪ |
| የሰንደቅ ዓላማው ምሥጢር፤ | ፷፫ |
| ሦስተኛው ቃል ኪዳን፡- ኪዳነ መልከ ጼዴቅ፤ | ፷፬ |
| ይህ ኪዳን፡ የኢትዮጵያዊነት ግንድ ስለመኾኑ፤ | ፷፭ |
| የኢትዮጵያዊነት ምሥጢር፤ | ፷፮ |
| የዲያብሎስ ሐሰት መፈራረስ አለበት፤ | ፸፩ |

# ማ ው ጫ

**አርእስት** **ገጽ**


አራተኛው ቃል ኪዳን:- ኪዳነ አብርሃም፤ ፸፪

ኢትዮጵያውያን: እውነተኞቹ የአብርሃም ልጆች፤ ፸፫

አምስተኛው ቃል ኪዳን:- ኪዳነ ሙሴ፤ ፸፭

የጽላትና የታቦት ምሥጢር፤ ፸፮

የብሉዩና የአዲሱ ኪዳናት "ጽላትና ታቦታት" የተለያዩ ስለመኾናቸው፤ ፹፩

ኢትዮጵያ: ስለታቦተ ጽዮን ፍለጋ ስትፋረድ! ፹፫

ስለአዲስ ኪዳኑ ታቦት አገልግሎት፤ ፹፮

በታቦት የሚፈጸመው አምልኮ: "በመንፈስና በእውነት" ስለመኾኑ፤ ፹፰

በታቦት የሚፈጸመው አምልኮ: "ባዕድ" እንዳይኾን ስለመጠንቀቅ፤ ፺፫

ኢትዮጵያ: በጽላትና ታቦት ላይ ስለሚፈጸመው በደል ስትፋረድ! ፺፭

እውነተኛ ኢትዮጵያዊ: ራሱ: ጽላትና ታቦት የመኾኑ ምሥጢር፤ ፺፱

ኢትዮጵያ: ሌላ አሕመድ ግራኝ ቢነሣ: በጽላት ላይ ስለሚደርሰው ምስቅልቅል: ስትፋረድ! ፩፻፩

ሙሴና ኢትዮጵያዊቷ ሲጳራ ፩፻፫

ስድስተኛው ቃል ኪዳን:- ኪዳነ ዳዊት፤ ፩፻፭

"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ማነው? ፩፻፭

የኢየሱስ ክርስቶስ ኢትዮጵያዊነት፤ ፩፻፮

ኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት የመኾኗ ምሥጢር፤ ፩፻፲

ሰባተኛው ቃል ኪዳን:- ኪዳነ ምሕረት፤ ፩፻፲፭

የቅዱስ ቁርባን ማኅተምነት፤ ፩፻፲፭

ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ÷ የአዲስ ኪዳኑ "አቤሜሌክ"፤ ፩፻፲፭

ለ"ብፅዕና" የሚያበቃው: ኢትዮጵያዊው ሃይማኖት፤ ፩፻፲፮

ምዕራፍ ፫

የመከራ ዘመናት እና መለኮታዊው ጥበቃ:: ፩፻፲፱

"ንቡረ እድ" ምንድር ነው? ፩፻፲፱

አኵስምና ዜናዋ፤ ፩፻፳፫

ኢትዮጵያዊው እንበረም፤ ፩፻፳፬

ከዔዛናና ሳይዛና: ወደአብርሃ ወአጽብሐ፤ ፩፻፳፮

ኢትዮጵያ: የግብፅ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ስትፋረድ! ፩፻፳፮

ሐሳዊው ይትበሃልና "አርቶዶክስ" የሚለው ቃል ጠንቅ፤ ፩፻፳፯

በጳጳሳት አሿሿም ላይ የተፈጸመ: የማይረሳ ደባ፤ ፩፻፳፱

ኢትዮጵያ: "ፍትሓ ነገሥት" ስለተባለው መጽሐፍ: ስትፋረድ! ፩፻፴፪

# ማ ው ጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ኢትዮጵያ: ስለትርጓሜዎቿ መዛባት: ግብፃውያንን ስትፋረድ! ፩፻፴፩
ኢትዮጵያዊዉን ካህን: ዮቶርን በሚመለከት፤ ፩፻፴፩
ኢትዮጵያዊቷን ንግሥት ማክዳን በሚመለከት፤ ፩፻፴፫
ኢትዮጵያውያኑን አቤሜሌክንና ባሮክን በሚመለከት፤ ፩፻፴፬
የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በሚመለከት፤ ፩፻፴፬
የኢየሱስ ክርስቶስን የልደት ቀን በሚመለከት፤ ፩፻፴፭
ኢትዮጵያ: ስለዘመን አቆጣጠርዋ: ግብፃውያንን ስትፋረድ! ፩፻፵
ኢትዮጵያ: ስለባሕረ ሐሳቧና ስለጌታ የልደት ቀን:
ግብፃውያንንና ክርስቲያኑን ዓለም ስትፋረድ! ፩፻፵፪
የጌታ የልደቱ ቀን: "አይታወቅም!" በሚል ምክንያት:
ከአረማውያኑ የበዓል ቀን ጋር ተጣምሮ መከበሩ፤ ፩፻፵፪
የጌታ የልደቱ ቀን: በዚያ የበረዶ ወራት ያለመኾኑ
ማረጋገጫዎች፤ ፩፻፵፫
የጌታ የልደት ጾምና በዓል: እንደሌሎቹ:
የቀመር ተውሳክ የሌላቸው መኾኑ፤ ፩፻፵፬
በአረማዊነት ባህል ላይ የተመሠረተው: የምዕራባውያን
የዘመን አቆጣጠር: ከኢትዮጵያውያኑ የሚለይበት
ባሕርይና የደረሰበት ቀውስ፤ ፩፻፵፭
የ"ሺሁ ዓመት" ምሥጢርና ፍጻሜው፤ ፩፻፶፩
ስለጌታ የልደት ቀን: የኢትዮጵያውያን ውሳኔ ምን
ሊኾን ይገባል? ፩፻፶፫
ስለገና ዛፍ: የአምልኮ ታሪክ፤ ፩፻፶፫
ኢትዮጵያ: ስለቅዱስ ቁርባን አቀራረብና አቀባበል:
ካህናቷንና ምእመናኗን ስትፋረድ! ፩፻፶፬
የካህኑ የእጅ መታጠብ ሥርዓት ምክንያት፤ ፩፻፶፮
የቁርባኑን ክልከላ የሚያጠናክረው ቃል: ከነድርጊቱ፤ ፩፻፶፯
ኢትዮጵያ: የግብፅ ቤተ ክርስቲያንንና ጳጳሳቷን ስትፋረድ! ፩፻፷
ግብፃዊው አባ ቄርሎስ የፈጸሙት አሳዛኝ ድርጊትና
የአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ግብረ አበርነት፤ ፩፻፷፩
ኢትዮጵያ: በግብፅ ቤተ ክርስቲያንና "ስሎሞናዊ ዘር" በሚባለው
ወገን መካከል ስላለው ምሥጢራዊ ውል ስትፋረድ! ፩፻፷፫
ኢትዮጵያ: በልጆቿ ማንነት ላይ: የግብፅ ቤተ ክርስቲያን:
ስትፈጽም ስለኖረችው ደባ: ስትፋረዳት! ፩፻፷፬
ወደኢትዮጵያ የገቡት: ቅዱሳን ሰዎችና ቅዱሳት ቅርሶች:
የኢትዮጵያን ጀግኖች ልጆች ገድል ሲያጠናክሩ! ፩፻፷፭


**ምዕራፍ ፬**


ኢትዮጵያ የወረሰቻቸው ያዕመ ርስት ይዞታዎቿ እና
በእነዚህ ላይ ሳይቋረጥ የቀጠለው የጠላት እከይ:: ፩፻፸
መልካሚቱ የሕይወት መመሪያ፤ ፩፻፸

# ማ ው ጫ


**አርእስት** **ገጽ**

ኢትዮጵያ፡ የዓለም መንግሥታትን ስትፋረድ! ፩፻፸፫
እውነተኛዋ ኢትዮጵያና እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን፤ ፩፻፸፬
ኢትዮጵያ፡ "እርሞ ነን" የሚሉትን ልጆቿን ስትፋረድ! ፩፻፸፭
ኢትዮጵያ፡ ትውልዷን ስትፋረድ! ፩፻፹
ሦስቱ የቀሩ ሕያዋን ውርሶች፤ ፩፻፹
የሦስቱ መለኮታውያን ማኅተሞች ሕያዋን መገለጫዎች፤ ፩፻፹፩
የኢትዮጵያዊነትና የኢትዮጵያ አንድነት፡
እውነተኞች ምሳሌዎች፤ ፩፻፹፫

ምዕራፍ ፰

ምክርና ማስጠንቀቂያ! ፩፻፹፭
ኹለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳይረሳ! ፩፻፹፭
ንስሓ፥ አምጻኤ ፍሥሓ! ፩፻፹፮

ምዕራፍ ፱

የኢትዮጵያውያን የቅዱሱ ኪዳን ጸሎቶች:: ፩፻፹፯
ሀ. የሃይማኖት ጸሎታቸው፤ ፩፻፹፯
ለ. የቃል ኪዳን ጸሎታቸው፤ ፩፻፹፱
ሐ. ለጌታ የሚቀርብ የምስጋና ጸሎታቸው፤ ፩፻፺
መ. ለእመቤታችን የሚቀርብ የሰላምታ ጸሎታቸው፤ ፩፻፺፩

ምዕራፍ ፲

ለመኾኑ፡ "የዚች *የእግዚአብሔር እውነት ልኡክ ነኝ*"
የሚለው፡ እርሱ ማነው? ፩፻፺፪
ለእግዚአብሔር ውለታ፥ በግል የቀረበ የምስጋና ሃሌታ! ፩፻፺፬

## ክፍል ኹለት

በእግዚአብሔር እውነት ላይ፡ በሥውር የተፈጸመው ክህደት፥
በቅርቡ የተረኰሰው መለኮታዊ እሳት፥
ያቀጣጠለው አስደንጋጭ መቅሠፍት! ፩፻፺፮
ከምስተር ካርል ፊልፖትስ ናፍታሊ የተጻፈው ደብዳቤ -በእንግሊዝኛ፤ ፩፻፺፱
መግቢያ፤ ለዚህ መጽሐፋዊ መልስ መንሥኤ የኾነው ደብዳቤ፤ ፪፻፫
መቅድም፡ ለዚህ መጽሐፋዊ መልስ፤ ፪፻፮

ምዕራፍ ፩

የፍሬ ጉዳዩ፡ መሠረታውያን መንሥኤዎች:: ፪፻፲፪
ኢትዮጵያ፡ "ራስ ተፈሪያውያን"ን፡ በእግዚአብሔር
እውነት ስትፋረድ! ፪፻፲፪
ስለራስ ተፈሪያውያን አጭር ሐተታ፤ ፪፻፲፫
መልሱ፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው! ፪፻፲፬
እንክርዳድ ዘሪው ጠላት፤ ፪፻፲፭
በቍስል ላይ ቍስል፤ ፪፻፲፮

# ማ ው ጫ


**አርእስት** **ገጽ**

ምዕራፍ ፪

ሥርዓተ ንግሥ፡ በቤተ ክርስቲያን የመፈጸሙ ምሥጢር። ፪፻፲፰

ኢትዮጵያ፡ ስለአምላክነትና ስለ"ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" ስትፋረድ! ፪፻፲፰

"ሥዩመ/ሥይምተ እግዚአብሔር" ተብሎ፡ ለአጼነትና ለንግሥትነት የመብቃት ምሥጢር፤ ፪፻፳፬

ምዕራፍ ፫

ተወቃሹ ማነው? ፪፻፳፯

አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ የተቀቡ "ሥዩመ እግዚአብሔር ናቸው፤ ፪፻፳፯

ከ"አጼነቱ" ክብርና ሥልጣን ጋር ያለው ተጠያቂነት፤ ፪፻፳፱

"ድፍረት!" የትኛው ዓይነት? ፪፻፴፪

ምዕራፍ ፬

የመጨረሻው አጼ፡ አሳዛኝ ፍጻሜ እና ጦሱ። ፪፻፴፬

ኢትዮጵያ፡ ስለቅዱሱ ኪዳኗ ስትፋረድ! ፪፻፴፬

የገድል ተሳታፊነት፥ ገና በልጅነት፤ ፪፻፴፰

ስለመጪው መከራ የተናገረው መጽሐፍ፡ በራሱ የደረሰበት መከራ፤ ፪፻፴፰

ለኃላፊነት አገልግሎት መጠራት፤ ፪፻፵፫

መፍትሔው ንስሐ ነበር፤ ፪፻፵፬

ከሰው ብልህነት፡ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይበልጣል፤ ፪፻፵፯

ኢትዮጵያ፡ እጨጌ ቴዎፍሎስን ስትፋረድ! ፪፻፵፯

የኹለት ብልሆች ብልጠት ሲነጻጸር፤ ፪፻፶፪

ከቤተ መንግሥት፡ ወደቤተ ሞቅሕ፤ ፪፻፶፬

በእሥር ቤት የተሰማው ተአምር፤ ፪፻፶፯

ምዕራፍ ፭

የቅዱሱ ኪዳን መለኮታዊ አማናዊነት፥ በእውን ያሳየው ትንግርት። ፪፻፷

ኢትዮጵያ፡ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅትን ስትፋረድ! ፪፻፷፪

ኢትዮጵያ፡ ያሴሩባትን የዓለም መንግሥታት ስትፋረድ! ፪፻፷፬

ኢትዮጵያ፡ ኤርትራን በሚመለከት፡ ደመኞቿን መንግሥታትና የትግራይ ልጆቿን ስትፋረድ! ፪፻፷፯

ምዕራፍ ፮

በኢትዮጵያዊ የተዋሀዶ ስውነት፥ የኹለት ባሕርያት ከሥተት፥ ጽኑ አደገኛነት። ፪፻፸፩

የምዕራባውያን ሥርዓተ መንግሥት፤ ፪፻፸፩

የዕብራውያን ሥርዓተ መንግሥት፤ ፪፻፸፩

የኢትዮጵያውያን ሥርዓተ መንግሥት፤ ፪፻፸፫

ኢትዮጵያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ታማኝነት ስትፋረድ! ፪፻፸፬

ኢትዮጵያ፡ የምዕራባውያንን ክርስቲያንነት ስትፋረድ! ፪፻፸፯

# ማ ው ጫ

| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ኢትዮጵያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን አመራር ስትፋረድ! | ፪፻፷፰ |
| የአመራሩ ቀውስ፡ በቤተ ክህነት ላይ ያስከተለው ችግር፤ | ፪፻፸ |
| ኢትዮጵያ፡ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱሳውያንን ስትፋረድ! | ፪፻፸፪ |
| ኢትዮጵያ፡ ፀረ ማርያሞችን ስትፋረድ! | ፪፻፸፫ |
| ኢትዮጵያ፡ አስተምራ ያሳደገቻቸውን ልጆቿን ስትፋረድ! | ፪፻፸፭ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለገዳምና ስለ"Cathedral ካቴድራል" ስትፋረድ! | ፪፻፹፩ |
| ኢትዮጵያ፡ ባዕዳን የሃይማኖት ልኡካንን ስትፋረድ! | ፪፻፹፭ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለእውነተኛ ልጇ፡ ስለአለቃ ዘካርያስ ስትፋረድ! | ፪፻፹፮ |
| የሼህ ዘኸርያ ማንነት፤ | ፪፻፹፮ |
| የሼህ ዘኸርያ ተልእኮ፤ | ፪፻፹፰ |
| የሼህ ዘኸርያ ገድል፤ | ፪፻፹፰ |
| የሼህ ዘኸርያ የድል አክሊል፤ | ፪፻፹፱ |
| ኢትዮጵያ፡ አድቬንቲስቶችን ስትፋረድ! | ፫፻ |
| የአድቬንቲስቶች ስሑት አገባብና መሠሪ ድርጊት፤ | ፫፻፩ |
| የድሉን አክሊል፡ ወደሽንፈት ደለል፤ | ፫፻፪ |
| ሐሳዊው ዘመቻ ተፋፍሞ ሲካኼድ፤ | ፫፻፫ |
| የአለቃ ዘካርያስ ልጆች አቤቱታ ሲሸነገል፤ | ፫፻፬ |
| የታመነ ተመልካችን ያጣ ቤተ መንግሥት፤ | ፫፻፭ |
| የውድቀቱ መቃረቢያ፡ አመልካች ድርጊት፤ | ፫፻፮ |
| ግራ የሚያጋባና አደናጋሪ ምግባር፤ | ፫፻፯ |
| ኢትዮጵያ፡ እስላሞችን ስትፋረድ! | ፫፻፯ |
| የመሐመድ የ"አደራ" ቃል፤ | ፫፻፱ |
| የጊዜው የእስላሞች አዝማሚያ፤ | ፫፻፲ |
| ለእስላሞች፡ ሃይማኖታዊ ማስጠንቀቂያ! | ፫፻፲፪ |
| የአኩስም ነገር፡ እስከመቼ? | ፫፻፲፫ |
| ኢትዮጵያ፡ የዛሬዎቹን የትግራይ ልጆቿን የምትፋረድበት፡ ሌላው አስተዛዛቢ ሙከራ፤ | ፫፻፲፭ |
| ለኢትዮጵያውያን፡ ሃይማኖታዊ ማስጠንቀቂያ! | ፫፻፲፮ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለቤተ ክህነቷ ጥቃት ስትፋረድ! | ፫፻፲፮ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለበጌምድርና ጎጃም ስትፋረድ! | ፫፻፳ |
| በዝምታ የሚፈጸም፡ የጳጳሳት ኃላፊነት፤ | ፫፻፳፩ |
| የጽሕፈት ቤት እንኳ አለመኖር፤ | ፫፻፳፪ |
| የማይጣጣም ድርጊት፤ | ፫፻፳፪ |
| ኢትዮጵያ፡ ስለቤተ ክህነቷ ግብርና ቀረጥ ከፋይነት ስትፋረድ! | ፫፻፳፫ |
| የባለ"ሲሶዋ መንግሥት" የሰሞን መሬት ገቢ፤ | ፫፻፳፫ |
| ጨርሶ የማዳከሚያው አዋጅና ጦሱ፤ | ፫፻፳፭ |
| የባለ"ሲሶዋ መንግሥት" የቤት ኪራይ ገቢ፤ | ፫፻፳፮ |
| የስቅላቱ ገመድ፡ ማነቀው ሲታገድ፤ | ፫፻፳፯ |

# ማ ው ጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ኢትዮጵያ፡ የአጼዎን፥ የጳጳሳቷንና የምሉካኗን ሃይማኖትና ምግባር ስትፋረድ! ፫፻፳፰
    የተግሣፀ ምልክትነት፤ ፫፻፳፱
ኢትዮጵያ፡ ምንኵስናንና ጵጵስናን ስትፋረድ! ፫፻፴
    የጳጳሳት የተሳሳተ ቅሬታና ሕገወጥ ድርጊት፤ ፫፻፴፩
ኢትዮጵያ፡ የዛሬውን እጨጌ፡ አባ ጳውሎስንና መሰሎቻቸውን ስትፋረድ! ፫፻፴፫
    ገለልተኛው አገልግሎት የተጀመረበት ሥራ፤ ፫፻፴፫
    በስደቱ መግቢያ፡ በናይሮቢ የተፈጸመ ግዳጅ፤ ፫፻፴፬
    የግእዝ ቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ ውጥን፤ ፫፻፴፭
    መሥዋዕትነት የተከፈለበት ሽምግልና፤ ፫፻፴፮
    ሰብአዊ ማንነት ሲለዋወጥ፤ ፫፻፴፯
    ከአሜሪካኑ ነዋሪዎች ጳጳሳት የተመለሰ፡ ያልተጠበቀ ውለታ፤ ፫፻፴፱
    ከደርጉ "ሲኖዶስ" የተላለፈ፡ "ምሥጢራዊ ውለታ"፤ ፫፻፵
    የጳጳሳቱ "እውነተኛ ማንነት" እየተጋለጠ ሲወጣ! ፫፻፵፪
    ዘረኝነት ወይም ጐሠኝነት ባለበት፡ ኢትዮጵያዊነት አይኖርም፤ ፫፻፵፫
ኢትዮጵያ፡ ዘመናውያን ባለማዕርግ ምሁራንን ስትፋረድ! ፫፻፵፭
    የሰዎች ትምህርት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ እንዳይሠለጥን፤ ፫፻፵፮
    የጃፓኑ ታሪካዊ "አያድርስ" ምሳሌነት፤ ፫፻፵፯
    የአባ ጳውሎስ፡ የባዕዳኑ የትምህርት ማዕርግ እንዳያዘናጋ! ፫፻፶
ኢትዮጵያ፡ ጳጳሳቷን ስትፋረድ! ፫፻፶፩
    የጵጵስና ሹመት ዓላማና ተግባር፤ ፫፻፶፩
    በደርግ በታሠሩትና ባልታሠሩት "አባዎች" ዘንድ የታየ ጉድ፤ ፫፻፶፪
    "ብፁዕ" እና "ቅዱስ" ለመባል፡ የሚያስፈልጉት መሥፈርታት፤ ፫፻፶፫
    የሆሣዕና ሥርዓት አርአያነት፤ ፫፻፶፬
    የጵጵስና ሕይወት፡ መንፈሳዊነቱን እንዳይለቅ፤ ፫፻፶፭
    የመጻሕፍተ መነኰሳቱ ትንቢት፡ ደርሶ ማየት፤ ፫፻፶፭
ኢትዮጵያ፡ ስለአጼ ኃይለ ሥላሴ የተቀባ ሰውነት ስትፋረድ! ፫፻፶፮
    ይሉኝታና ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለበት ድርጊት፤ ፫፻፶፯
    ከክርስቶስ የሕይወት ቃል ይልቅ፡ የዲያብሎስ የሞት ሕግ የሰፈነበት ሥርዓት፤ ፫፻፶፱
    የቤተ ሕዝቡ ተጠሪዎች፡ በመለኮታዊው ሥልጣን፡ ዳግመኛ ከመጠየቅ አያመልጡም፤ ፫፻፷

# ማ ው ጫ


| አርእስት | ገጽ |
|---|---|
| ኢትዮጵያ፡ ስለአልጋ ወራሽ አስፋ ወሰን ስትፋረድ! | ፫፻፳፩ |
| የአንድ መነኩስ/ጳጳስ ሌላው አሳዛኝ ግብር፤ | ፫፻፳፩ |
| የአጼነቱ መለኮታዊ ሥርዓት፡ በሰዎች ሕገወጥ አሠራር ሊፋለስ አይችልም፤ | ፫፻፳፪ |
| ኢትዮጵያ፡ ሥርዓተ ሢመተ ጵጵስናን ስትፋረድ! | ፫፻፳፬ |
| ጵጵስናን ለመነኩሳት ብቻ ወስኖ የሰጠ ማነው? | ፫፻፳፬ |
| ኢትዮጵያ፡ በጦር ኃይል ድርጅት የሚያምኑ ልጆቿን ስትፋረድ! | ፫፻፳፮ |
| ለጸጥታና ለጦር ዝግጅት የፈሰሰው ገንዘብ፡ ያስገኘው መራራ ፍሬ፤ | ፫፻፳፮ |
| ኢትዮጵያ፡ የቲቶን ዩጎዝላቪያና መሰሎቿን ስትፋረድ! | ፫፻፳፯ |
| የማይጣጣም፡ የሃይማኖትና የምግባር እንቆቅልሽ፤ | ፫፻፳፱ |
| ኢትዮጵያ፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴን ሕገ መንግሥት ስትፋረድ! | ፫፻፴ |
| መለኮታዊዉን ሕገ መንግሥት፡ ሰብአዊው አይተካውም፤ | ፫፻፴፩ |
| "ድርጊት፡ በውጤቱ ይጸድቃል!" የሚለውን ፈሊጥ ኢትዮጵያ አትቀበለውም፤ | ፫፻፴፪ |
| ለመጨረሻው ትዝብት መጋለጥ | ፫፻፴፫ |
| **ምዕራፍ ፯** | |
| ኹለተኛው የዓለም ጦርነት፡ የመጣበት ምክንያት፥ በመለኮት ዳኝነት። | ፫፻፴፬ |
| ኢትዮጵያውያን፡ የቅዱሱ ኪዳን ግዳጃቸውን ሲዘነጉ፤ | ፫፻፴፬ |
| ኢትዮጵያ፡ የማይጨውን ጦር ሜዳ ስትፋረድ! | ፫፻፴፭ |
| አጼ ኃይለ ሥላሴ፡ በጀኔቫው ቃል ኪዳን መታለላቸው፤ | ፫፻፴፮ |
| በቅዱሱ ኪዳን መታመን ሲቀር፤ | ፫፻፴፮ |
| ኢትዮጵያ፡ የጀኔቫውን የዓለም መንግሥታት ማኅበር ስትፋረድ! | ፫፻፴፯ |
| የክህደት ኮሶና ንግርት የመላበት የጀኔቫው ዋንጫ፤ | ፫፻፴፱ |
| የስደቱ ጽዋ ያስገኘው የንስሓ በረከት፤ | ፫፻፵ |
| የንስሓው ፍሬ፡ በከሃዲዎቹ ላይ ያወረደው በቀል፤ | ፫፻፵፪ |
| መለኮታዊው ፍትሕ፥ ጥበብና ኃይል፡ ከሰብአዊው ይልቅ እጅግ ይበልጣል፤ ይረቅቃልም፤ | ፫፻፵፬ |
| መለኮታዊቷ የድል አክሊል፤ | ፫፻፵፭ |
| መፈጽም፤ ለዚህ መጽሐፋዊ መልስ። | ፫፻፵፮ |
| **ማጠቃለያ ምዕራፍ** | |
| ኢትዮጵያ፡ ስለባህሏ ጥበቃ፡ የዛሬውን ትውልድ ስትፋረድ! | ፫፻፵፱ |
| "የጨው ክምር ሲናድ፡ ምኝ ይስቃል፤ ብልህ ያለቅሳል!" | ፫፻፵፱ |
| የመጀመሪያዎቹ ሰዎችና የእባቢቱ ጭውውት፤ | ፫፻፵፱ |
| በቀራጥ ሕዝብ ዘንድ፡ መልካሙ ኹሉ ይቻላል! | ፫፻፶ |
| ስለሃይማኖታዊው ሥነ ምግባር፡ የሕዝቦች የተለያየ ግምት፤ | ፫፻፶ |

# ማ ው ጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ኢትዮጵያ፡ ስለመከባበር ባህሏ፡ ትውልዷን ስትፋረድ! ፫፻፺፩
ኢትዮጵያ፡ ስለሰላምታ አሰጣጧ ሥርዓት፡ ትውልዷን ስትፋረድ! ፫፻፺፪
የእጅ መንሣት ሥርዓት፡ ትርጓሜና ሐተታ፤ ፫፻፺፪
የሰላምታ ቃሎቻችን፡ መልእክት አላቸው፤ ፫፻፺፬
ኢትዮጵያ፡ ስለአለባበሷ ሥርዓት፡ ትውልዷን ስትፋረድ! ፫፻፺፭
ባለቤቱ፡ በቤቱ ባይተዋር ሲኾን፤ ፫፻፺፭
"ባለኩታው" ኢትዮጵያዊ፡ ሲናቅና ሲዋረድ፤ ፫፻፺፮
ሌላው አሳዛኙ "አጋጣሚ"፤ ፫፻፺፮
የአንድ ኢትዮጵያዊ፡ የጀግንነት ድርጊት፤ ፫፻፺፯
ኢትዮጵያዊው ልብስ፡ "ጸዓዳ" (ነጭ) የኾነበት ምክንያት፤ ፫፻፺፱
በዚህ ምግባር፡ ተከታይ ያገኘው ማነው?
ኢየሱስ ክርስቶስ? ወይስ ዲያብሎስ? ፬፻
ኢትዮጵያ፡ ስለቋንቋዋና ፊደሏ ትውልዷን ስትፋረድ! ፬፻፩
የግእዝን ፊደል ከነአኀዙ ለማጥፋት የሚካኼደው ዘመቻ፤ ፬፻፪
ግእዝን ከነፊደሉ ያተረፉት ኢትዮጵያውያን ጀግኖች፤ ፬፻፫
የጀግና ልጅዬው ገድል፤ ፬፻፫
የጀግና አባትዬው ገድል፤ ፬፻፯
ኢትዮጵያ፡ ስለሆህያቷ ሥርዓት፡ ትውልዷን ስትፋረድ! ፬፻፲
"ሆህያት ይቀነሱ!" የሚያሰኙ በቂ ምክንያቶች አሉ ወይ? ፬፻፲
የግእዝ ማንነትና ምንነት፤ ፬፻፲፪
የመደበኞቹ ሆህያት፡ ምሥጢራዊ ትርጓሜ፤ ፬፻፲፪
ስለግእዝ ሆህያት አጭር ሐተታ፤ ፬፻፲፬
የሆህያቱ ፍጹምነትና ምሉእነት፤ ፬፻፲፬
የግእዝን ሆህያትና አኀዛት ማጥፋት ለምን አስፈለገ? ፬፻፲፮
ባለአደራዪቱን ራሷን፡ እንደአጥፊ ሲያስቆጥሩዋት፤ ፬፻፲፯
በባዕዳኑ ስለተፈናቀሉት ኢትዮጵያኛዎቹ ቃላትና አኀዛት፤ ፬፻፲፱
ኢትዮጵያ፡ የሊቃውንቷን ምግባር ስትፋረድ! ፬፻፳
በሰብሳቢው ማንነት የታወቀው፡ የቤተ ክህነት
ሊቃውንት ጉባዔ ተጠያቂነት፤ ፬፻፳
የሊቃውንት ጉባዔ ግዳጅ ሳይፈጸም መቅረቱ፤ ፬፻፳፩
የሃይማኖትን አቋም የሚያናጋ ደማሚት፤ ፬፻፳፪
ስለሰበካ ጉባዔ የማውቀውን ለመመስከር፤ ፬፻፳፫
ለእሥር ቤቱ ገጸ በረከት የተሰጠው ምላሽ፤ ፬፻፳፭
ኢትዮጵያ፡ በአጠቃላይ ትውልዷን ስትፋረድ! ፬፻፳፮
ማየ አይኑ (የጥፋቱ ውኃ) አጥለቅልቆ እንዳያሰጥም፤ ፬፻፳፮
ለመከሊቶቹ ባለቤት ስለምንሰጠው ምላሽ ተዘጋጅተናል? ፬፻፳፯
ጥቃታቸውን የሚወጡትን ጉበዞቹንማ አየናቸው! እኛሳ! ፬፻፴

# ማ ው ጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ለአንባቢው የቀረበ-የሙገሳ ቃል:: ፩፻፴፭
በኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግሥት አገልግሎት
መመሪያ ሥርዓት ፩፻፴፰
የኢትዮጵያውያን የቅዱሱ ኪዳን መዝሙር ፩፻፵፫
" የመከራ ጊዜ " ፩፻፵፮
" የሰንደቅ ዓላማ " ፩፻፵፯
ተጨማሪ አርእስት:: ፩፻፶፱
ይህ መልእክት በጽሑፍ ስለደረሳቸው: በመላው ዓለም ስለሚገኙ:
የየአገሩና የየመንግሥቱ፥ የየቤተ ክርስቲያኑና የየሃይማኖቱ
መሪዎች፥ የመንፈሳዊና የሥጋዊ: ብሔር-አቀፍ፥ አድያም-አቀፍና
አህጉር-አቀፍ ድርጅቶች አለቆች፥ እንዲሁም: አግባብ ስላላቸው
የግል ተቋሞች ኃላፊዎችና ግለሰቦች የስም ዝርዝር መግለጫ፤ ፩፻፶፱
ለዓይነት የቀረቡ የመሸኚያ እና የመልስ ደብዳቤዎች፤ ፩፻፶፱
መልእክቱ የደረሳቸው መሪዎች ስም ዝርዝር፤ ፩፻፷፫
ጥቅሶችና ማብራሪያዎች፤ ፩፻፷፱
የኢትዮጵያዊው ፊደል ሆህያትና አኀዛት፤ ፩፻፸፫
በባዕዳን ተዘውትረው የተገፉ ኢትዮጵያኛ ቃላት፤ ፩፻፸፱
"መቆየት!" ፩፻፹፯
ለባለውለታዎች የቀረበ ወረታ ፩፻፹፯


\+ + +

# መቅድም

## የዚህ መጽሐፍ አጠቃላይ ዓላማ

ከዚህ ቀደም ብሎ፡ በ፲፱፻፺፭ ዓ. ም. በታተመው፡ *"ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"* በሚለው ድርሰት ውስጥ፡ በክፍል አንድ፡ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፍረጃ!" የሚለው ይህ መጽሐፍ፡ Ethiopia: The Classic Case በሚል ትርጉም፡ በ፲፱፻፺ ዓ. ም. በእንግሊዝኛ ታትሞ መውጣቱን ምክንያት በማድረግ፡ በዘመኑ ትውልድ ላይ፡ የከበዱ ኃይለ ቃላትን የሠነዘረ፡ ዝርዝር መግለጫ የተሰጠበት መኾኑ ይታወሳል። በዚያ፡ በእንግሊዝኛው ዕትም ውስጥ ከተገለጹት ቁም ነገሮች በላይ፡ በተጨማሪ፡ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች አስፈላጊ የኾኑ፡ ሰፋፊ ሐተታዎች ታክለውበት፡ ይህ መጽሐፍ፡ እነሆ፡ በዚህ፡ በኢትዮጵያዊ መልኩ ተጠናቅቆ፡ ለሕዝባዊ ንባብ በቅቷል።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው መልእክት፡ ሰው-ሠራሽ ከኾነችውና ስለኾነችው፡ ወይም ዓለማውያን የታሪክ ጸሐፊዎችና ምሁራን፡ እንደዚያች አስመስለው፡ ካቀረቡዋትና ስላቀረቧት፡ ወይም በዛሬው ኹኔታ፡ በገሃድ እንደሚታየው፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፡ በሥጋውያን የሥነ መንግሥት ፈሊጠኞች (Politicians) ከተፈጠረችውና ስለተፈጠረችው፡ "አስመሳዪቱ ኢትዮጵያ"፡ የተባለፈ ወይም የሚናገር አይደለም።

ይህ መልእክት፡ እግዚአብሔር ከሠራት፡ ጥንታዊትና ኪዳናዊት፥ ሕያውትም ከኾነችውና ስለኾነችው፡ ስለእውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ፡ የተባለፈና የሚናገር ነው። እርሷም፡ ባህልና ቅርስ ባላቸው፡ በሠለጠኑት የዓለም አገሮች፡ ማለትም፡ በጥንታውያኑም፥ በማእከላውያኑም፥ በዘመናውያኑም ዘንድ፥ ደግሞ፡ ሃይማኖተኞች በኾኑት የዓለም ሕዝቦች፡ ማለትም፡ በአይሁድና በክርስቲያኖች፥ በእስላሞችና በሌሎቹ እምነቶች ተከታዮች ዘንድ፥ እንዲሁም፡ መለኮታዊዉን ወይም መለካዊዉን፥ አምባገነናዊዉን ወይም ሕዝባዊዉን ፈለግ የተከተለ ሥርዓተ መንግሥት ባላቸው ዘንድ ኹሉ፡ በዚህ ማንነቷ ታውቃ የኖረችውና ወደፊትም የምትኖረው ናት።

የመልእክቱ የመጀመሪያ ክፍል ዓላማ፡ በቅድሚያ፡ ስለኢትዮጵያ፥ ስለኢትዮጵያውያንና ስለኢትዮጵያዊነት ለማያውቁና ማወቅ ለሚገባቸው፡ እውነቱን፡ ያውም፡ የእግዚአብሔር በኾነችው እውነት ላይ በመመሥረት፡ በትክክል ማሳወቅ ነው። ከዚህ ጋር፡ ኢትዮጵያን በሚመለከት፡ አንዳች የመቀራረብ ወይም የመጠቀም አዝማሚያ ያላቸው ኾነው፡ ነገር ግን፡ በእርሷ ላይ በተቃዋሚነት ወይም በአጉል አስተሳሰብ በተፈጠረ ተቃራኒ ስሜት የተነሣሡ ቢኖሩ፡ ለየራሳቸው ደኅንነት ሲሉ፡ በዚህ ረገድ የተከተሉትን አቋማቸውን እንደገና እንዲመረምሩና ከተሳሳተው መንገዳቸው እንዲመለሱ የሚያሳስብ፡ ተግሣፅ አዘል ምክር ይገኝበታል።

በመጨረሻም፡ ኢትዮጵያንና እርሷ ስትጋደልላቸው የኖረችውን፡ መለኮታውያን ይዞታዎቿን አፈራርሰው ለመደምሰስ፡ በግልጽና ወይም በሥውር፡ ታጥቀው የተነሡባትን ባላጋራዎቿን ደግሞ፡ ስለሚጠብቃቸው እጅግ አስፈሪ ፍዳ በማስጠንቀቅ፡ በኃያሉ እግዚአብሔር ፊት፡ ንስሓ ገብተው፡ ከዚህ ዓላማቸው ይመለሱ ዘንድ መማጸን ነው።

# ኢትዮጵያ:

የመልእክቱ ኹለተኛ ክፍል: ቀደም ብላ በተወሳችው: በእግዚአብሔር እውነት ላይ: ሰዎች: በሰብአዊ ስሑትነታቸው: በረቂቅ ብልጠትና ስልት ከፈጸሙት የክህደት ዓመፅ የተነሣ: ስለነደደው መለኮታዊ ቁጣ ያትታል:: ይኸው ኹለተኛው ክፍል እንዲጻፍና በዚህ ዕትም ውስጥ ታክሎ እንዲወጣ ለማድረግ ምክንያት የኾነው መነሻ: ከአንድ ራስ ተፈሪያዊ: የተጻፈልኝ የመልስ ደብዳቤ ነው::[፩]

ታዲያ÷ የጃማይካ ተወላጅ የኾነው ይህ ሰው: የዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያው ክፍል ደርሶት ኖሮ: በዚያ ጽሑፍ ውስጥ ከተጠቀሱት ዐበይት ጉዳዮች መካከል: አንደኛውን በሚመለከት: ብርቱ የኾነ ሃይማኖታዊ ክህደትን የተመላ የነቀፌታን ቃል: በዚሁ ደብዳቤው ውስጥ አክሎ ስለላከልኝ: ለዚህ: ከባድ ኑፋቄው: የተሰጠው ተገቢ ምላሽ: በመጽሐፉ ኹለተኛ ክፍል ተዘርዝሮና ተጠቃልሎ ሠፍሩዋል::

የዚህ: እንደፍላፃ የተቆጠረው ደብዳቤ: ብርሃናዊ ቅጂና ትርጉም: ለመጽሐፉ ኹለተኛ ክፍል መግቢያ ኾኖ ቀርቧል:: ያም በገጽ ፩፻፺፱-፪፻፮ ላይ ይገኛል::

ኢትዮጵያን በሚመለከት: አንዳች የመቀራረብ ወይም የመጠቀም አዝማሚያ ባላቸውና በሌላቸው የተወሰኑ ወገኖች በኩል: በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ማንነት÷ እንዲሁም ሕያዋን በኾኑት ውርሶቻችን ላይ: ኾነ ተብሎ ወይም በሌላ ኅጂ ዓላማ የሚካሄደው ልዩ ልዩ የማሳሳትና የፈጠራ÷ የማወናበድና የማስመሰል ሙከራ: እያየለ መቀጠሉ: እነሆ በገሃድ ይታያል:: ስለዚህ ሙከራውን ኹሉ በማክሸፍ: ሐሰቱን በእውነት የማጥራቱ ብቻ ሳይኾን: ጠማማውንም: በርቱዕ ብዕር የማቃናቱ ተግባር ጭምር: እጅግ አስቸኳይ ኾኖ ተገኘ:: እነዚህን ኹለት ክፍሎች የያዘው: ይህ መልእክት: እንዲህ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ እንዲወጣ: ሌላ አማራጭ የሌለው: ፍጹም አስፈላጊ ግዴታ የኾነው: በዚህ ምክንያት መኾኑን ልገልጽ እወድዳለሁ::

እንግዴህ: "ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት: መልስ ለመስጠት: የእውቀቱን ሥልጣን የያዝን እኛ ነን" ለሚሉ ምሁራን÷ እንዲሁም: ስለዚሁ አርእስተ ጉዳይ: በጥልቀት በመጻፍና የጥናት ምርምር በማድረግ ላይ ለሚገኙ ኹሉ: የማሳስበው: ይህ መጽሐፍ የያዘውን የእውነት ቁም ነገር በትክክል አጢነው እንዲገነዘቡትና ምናልባትም: ከዚህ እውነት የተዛባ የትምህርት ፈለግ ተከትለው እንደኾነ: በዚህ ረገድ: ተገቢውን እርማት በማድረግ: ፈለጋቸውን እንዲያስተካክሉ ነው::

ኢትዮጵያን የሚወድዱ ኹሉ÷ ደግሞም: ከዚችው አገራቸው ከፈለሱ በኋላ: ዝንተዓለም በምድር ላይ ተበትነው: የሚኖሩትና የትውልድ ሐረጋቸውን ስበው: ከኢትዮጵያ የዘር ግንድ ጋር በማያያዝ: "የእርሷ ተወላጆች ነን" የሚሉት ወገኖች÷ ራሳቸውን "ራስ ተፈሪያውያን" ብለው የሚጠሩት ጭምር: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከተከሠተችው እውነት: ጠቃሚ እውቀቶችን እንደሚቀስሙ ተስፋ እያደረግሁ: ሕይወታቸውን: ለዚህ ጸጋ ያበቁ ዘንድ እማጸናቸዋለሁ::

በዚህ መጽሐፍ፡ የእንግሊዝኛው ዕትም ውስጥ የሠፈሩት፡ መጀመሪያና ኹለተኛ የኾኑት፡ ኹለቱም፡ የመልእክቱ ክፍሎች፡ ይፋ በኾነ የደብዳቤ ቅጽ ተጽፈውና የደብዳቤ ማተብ (tembre ቴምብር) ተደርጎባቸው፡ አግባብ ላላቸው፡ በመላው ዓለም ለሚገኙ፡ ለየአገሩና ለየመንግሥቱ፥ ለየቤተ ክርስቲያኑና ለየሃይማኖቱ መሪዎች፥ የመንፈሳዊና የሥጋዊ፡ ብሔር-አቀፍ፥ አድያም-አቀፍና አህጉር-አቀፍ ለኾኑት ድርጅቶች አለቆች፥ እንዲሁም፡ ለየግል ተቋሞች ኀላፊዎችና ጥቂት ግለሰቦች ተልከዋል:: የተላከላቸው ባለአድራሻዎች ስም ዝርዝር፡ በመጽሐፉ ጥራዝ መጨረሻ፡ በገጽ ፩፻፸፭-፩፻፸፯ ላይ ተጽፎ ይነበባል::

ደብዳቤው በዚህ መልክ እንዲሠራጭ አስፈላጊ የኾነበት ምክንያት፡ አጠቃላይ ኃላፊነት ባለባቸው መሪዎች አማካይነት፡ መልእክቱ፡ ለየሕዝቦቻቸውና በሥልጣናቸው ሥር ለሚካኼዱት ድርጅቶች እንዲደርስ በማድረግ፡ "መላው የሰው ዘር፡ እንዳይጠፉ ለማዳን ይረዳል!" በሚል ዓላማ መኾኑን፡ እዚህ ላይ ሳልገልጽ አላልፍም::

መልእክቱ፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያኛ ብቻ ሳይኾን፡ በእንግሊዝኛ ጭምር ተዘጋጅቶና ታትሞ፡ ለእያንዳንዱ ሕያው ግለሰብ ሊደርሰው የተገባና የተመደበ በመኾኑ፡ ቅጂውን፡ ማናቸውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በቀላሉ ሊያገኘው እንዲችል የማድረግ ግዴታ እንዳለብኝ በጥልቅ ተሰማኝ፤ ይህም ሲኾን፡ የማናቸውንም ግለሰብ፡ የዕድሜ መጠንና የትምህርት ደረጃ፥ የአካል ጤንነትና የሀብት ይዞታ፥ የሙያ መስክና የማዕርግ ዕርከን፥ እንዲሁም፡ የዘር ወገንነትና የሃይማኖት አባልነት፥ የማኅበራዊ ኑሮ አቋምና የሥነ መንግሥት ዝንባሌ፡ በምንም ዓይነት፡ ልዩ አስተያየት ውስጥ በማስገባት እንዳይኾን የማረጋገጡን ኃላፊነት ባለመዘንጋት ነው::

በእንግሊዝኛ ተዘጋጅቶ የነበረው፡ ዋናው ተቀዳሚ ጽሑፍ፡ አንዳንድ ማስተካከያና ጥቂት እከላ ተደርጎበት፡ መልእክቱን በማጠቃለል፡ Ethiopia: The Classic Case በሚል ርእስ፡ በ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. (1997) ታትሞና በመጽሐፍ ቅጽ ተጠርዞ ሊሠራጭ በቃ! በዚያ፡ (በእንግሊዝኛው) መጽሐፍ መቅድም ላይ እንዳመለከትሁት፡ በዕትሙ ውስጥ የቀረቡት ሐተታዎችና የተገለጹት እውነታዎች፡ ከዚህ የሚከተሉትን፡ ኹለት ተልእኮዎች እንዲፈጽሙ ልባዊ ምኞቴ ነበር::

አንደኛው፡ አንባቢዎችና ከእነርሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው፡ ሰብአውያን ወገኖቻቸው ኹሉ፡ በእነርሱ አማካይነት፡ ስለኢትዮጵያና እርሷ ስለምትኖርበት፡ ስለቅዱሱ ኪዳን ይዞታዋ፡ እውነተኛውን እውቀት እንዲያገኙ መርዳት ነበር፤ ኹለተኛው ደግሞ፡ አንባቢዎችና በሕዝባዊ ኃላፊነት ተጠያቂዎች የኾኑት ኹሉ፡ የእግዚአብሔርን እውነትና እርሷ፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በዚህ መልእክት ውስጥ፡ በእውን የሰጠችውን የማስጠንቀቂያ ቃል በሚመለከት፡ እያንዳንዳቸው በግል፥ ኹሉም በጋራ፡ ያላቸው አቋም፡ በምን ዓይነት ኹኔታ ላይ እንደሚገኝ፡ የየራሳቸውን ድርሻ፡ እንደገና መላልሰው፡ በጽኑ እንዲመረምሩ፡ ማሳሰብ ነበር::

ይህ ማሳሰቢያ እንዳለ ኾኖ፡ በተለይ፡ ይህን፡ የኢትዮጵያኛውን ዕትም በሚመለከት፡ ከዚህ በታች ያለው ተጨማሪ ማብራሪያ፡ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎቼ ቀርቧል::

## በተለይ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች፡፡

ባለፉት ድርሰቶቼ ውስጥ እንደገለጽሁት፡ እኔ፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፥ ወደፊትም፡ በነፍሴና በሥጋዬ፥ በመንፈሴም፡ ያው፡ አባቶቻችንና እናቶቻችን፡ በኢትዮጵያ አጽንተውና ጠብቀው፡ በሕያውነት ያኖርዋት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ ነኝ! ከዚህ የተነሣ፡ የማስበው፥ የምናገረውና የምጽፈው፥ የማደርገውም ኹሉ፡ የእግዚአብሔርን እውነት በመከተል ብቻ ሊፈጸም እንደሚገባ አምናለሁ፡፡ ይህንም፡ ሌላው የሚስተው አይመስለኝም፡፡ እንግዴህ፡ እንዲህ እንደመኾኔ፡ የእኔ ተልእኮ፡ ይህች መንግሥት፡ ለሰው ልጆች ያበረከተችውን ሕይወት፡ በግልና በቤተሰባዊነት፡ ለራሴ እየኖርኋት፥ ባለኝ ዓቅም ደግሞ፡ ለሌሎች አስፈላጊውን ግልጋሎት እየሰጠሁ፥ ስለእርሷ፡ የሚሰማ ጆሮ ላለው ፈቃደኛ ሰው ኹሉ፡ ተገቢውን ምስክርነት፡ በቃልና በጽሑፍ መስጠት ነው፡፡ አዎን! ለእኔ፡ እስከሥጋ ሞቴ ድረስ፡ በቃል ኪዳን የተጠመድሁበት ተልእኮዬ፡ ይኼ ብቻ ነው፡፡ ዲያብሎስ፡ በበኩሉ፡ በእኔ ላይ፡ በሥውር የሚያናፍሰው፥ ወይም ተቃዋሚዎቼ፡ በሹክሹክታ የሚያሠራጩት የሐሜት ቃል ቢኖር፡ ያ፡ እነርሱ የሚጠየቁበት ነው፡፡ እኔ የማውቀው፡ ሌላ ዕቅድና ተልእኮ የለኝም፡፡

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ፡ በዚህ ተልእኮዬ መሠረት ላይ ታንፆ፡ በሚከተሉት ፍሬ ነገሮች ይጠቃለላል፡፡ ፩ኛ. "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት!" ስንል፡ ሕዝቧን የምታስተዳድረውና በሥነ ፍጥረት ጸጋዎቿ የምትጠቀመው፡ በእግዚአብሔር ሕግና ሥርዓት እየተመራች መኾኑን በይፋ ማሳወቃችን ነው፡፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና የተባሉ፡ ሦስት የአቋምና የአገልግሎት ዘርፎች ባሉት፡ በዚህ መለኮታዊ አስተዳደርና አመራር ውስጥ የሚከሠቱትን ጨለማና ሐሰት፡ ከነአበጋዛቸውና ሠራዊታቸው፡ በእግዚአብሔር የእውነት ፋና እያስወገደች፡ በብርሃኗ ፀዳል፡ ኹሉን ገላልጣ፡ ሥራዋ፡ በቅንነት እንዲካኼድ ታደርጋለች፡፡ ስለዚህ፡ በአገልጋዮቿና በተገልጋዮቿ፥ በአጠቃላይም፡ በልጆቿ መካከል ባለው አንድነት፥ እነርሱም፡ ከባዕዳን ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት፡ ሃይማኖታቸውንና ምግባራቸውን በሚመለከት፡ እንደዓለማውያንና እንደሥጋውያን ሰዎች፡ መወላወል፥ ማመንታት፥ ማለባበስ፥ መሸነጋገል፥ መፈራራት፥ መተማማት፥ መወሻከት፥ ማመንዘር (ወረተኛ መኾን ወይም ታማኝነትን መለዋወጥ)፥ ይሉኝታና አድር ባይነት፥ በኹለት መላስ መናገር ወይም በኹለት ቢላ መብላት፥ የመሳሰሉትንም ኹሉ ማካኼድ የለም፡፡ ራሳቸውን፡ ለእግዚአብሔር፥ ለቃሉና ለሕጉ፥ ለአምልኮቱና ለሥርዓቱ ያስገዛሉ እንጂ፡ እግዚአብሔርን፡ ስሙንና ሥልጣኑን፥ ምልክቶቹንና አገልጋዮቹን፥ ሃይማኖታዊ አቋሙንም፡ ለየራሳቸው የግልና የጋራ ዓላማቸው፡ መጠቀሚያና መሣሪያ አያደርጉም፡፡

፪ኛ. ይህች የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የተመሠረተችባቸው ድንጋዮች፥ የቆመችባቸው ምሰሶዎችና የተደመደመችባቸው ጉልላቶች አሏት፡፡ እነርሱም፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተዘረዘሩት፡ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ናቸው፡፡ ሕዝቧ፡ በሥጋም፥ በነፍስም፥ በመንፈስም፡ ፍጹም ሰላምን አግኝቶ፡ በዕድገት ጐዳና እየተራመደ፡ የብልጽግና ኑሮውን ያለሥጋት ሊቀጥል ይችል ዘንድ፡ እነዚህን ኪዳናት መጠበቅ፡ የመለኮታዊው ውል፡ ዋናው አንቀጽ ነው፡፡ እነዚህ ኪዳናት፡ በእግዚአብሔር በኩል፡ ምንጊዜም፡ በሚያስተማምን ይዘት፡ ተከብረውና ተጠብቀው ይኖራሉ፡፡

ነገር ግን፡ ተደጋግሞ እንደታየውና አሁንም እንደሚታየው፡ በቤተ ሕዝቧ በኩል ፈርሰው በሚገኙበትና የመፍረሳቸው ጽዋ ሞልቶ፡ መፍሰሱ በሚረጋገጥበት ጊዜ፡ የማይቀሩት፡ የታወቁት አራት መቅሠፍቶች ይመጣሉ:: እነዚህም፡ ረሃብ፥ በሽታ፥ ጦርነትና ስደት ናቸው::

፫ኛ. በአሁኑ ጊዜ፡ በተለይም፡ ከ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ጀምሮ፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታዊ ሥርዓትና ሕግ፡ ቀደም ብሎ፡ ባለው ዘመን፡ በሥውር፥ በኋላ ግን፡ በይፋ ፈራርሶ፡ እነዚህ፡ አራት መቅሠፍቶች፡ በአገሪቱና በሕዝቧ ላይ እየወረዱ ይታያል:: ለምን? ቤተ ሕዝቡ፥ ቤተ ክህነቱና ቤተ ምልክናው፡ ኹሉም በኅብረት፡ ሰባቱንም ቅዱሳት ኪዳናት ስላፈረሱ መኾኑ፡ በዚህና በሌሎቹ መጻሕፍቶቼ ውስጥ በሚበቃ ተብራርቷል:: ይህ፡ እየቀጠለ በመኼድ ላይ የሚገኘው አሳዛኝ ኹኔታ ተወግዶ፡ መልካሙ ጊዜ እንዲመጣ ከተፈለገ፡ የቃል ኪዳኑ አፍራሾች ኹሉ፡ "አዎን! በእርግጥ፡ እግዚአብሔርን በድለናል!" ብለው ጥፋታቸውን፥ በደላቸውንና ኃጢአታቸውን አምነው፥ ከዚህ የከፋት አካኼዳቸውም፡ በጸጸትና በንስሓ ተመልሰው፡ የቃል ኪዳን አምላካቸውን ይቅርታ መጠየቅ አለባቸው:: አዎን! ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር ጋር የመታረቁ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ከኹሉም ነገር ሊቀድም የሚገባው ነው::

፬ኛ. ፈጣሪያችን፡ በእውነተኛ ንስሐ፡ ወደእርሱ በምንመለስበት ጊዜ፡ ይቅር ይበለን እንጂ፡ ይህ ኹሉ ፈተናና መከራ፡ በአገሪቱና በሕዝቧ ላይ እየወረደ ያለው፡ በእግዚአብሔር በኩል የጎደለ ነገር ኖሮ ሳይኾን፡ ወደር በሌለው፡ በራሳችን ክፋትና በደል መኾኑን፡ ማለትም፡ ቅዱሳት ኪዳናቱ፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው በኩል፡ በዓመፅና በክህደት፥ በአመንዝራነትም፡ በመፍረሳቸው ምክንያት መኾኑን፡ ልናስተባብል አይቻለንም፤ አይገባንምም:: ይህን እውነት፡ በተጨባጭ ለማስረዳት፡ ከራሴና ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወይም ኢትዮጵያዊት ጀምሮ፡ እስከርእሰ ብሔሩ፡ እስከ አጼ ኃይለ ሥላሴ ድረስ፡ የተደረገውን ጥፋት፥ የተፈጸመውን በደል፥ የተሠራውን ኃጢአት፡ የየግለሰቦችን ስም ሳይቀር በመጥቀስ፡ ራሴ የማውቀውንና ከእውነተኛ ምንጭ ያገኘሁትን፥ ደግሞም፡ በጊዜው ሳላውቀው የቆየሁትንና የኋላ ኋላ የተረዳሁትን ገልጬ ጽፌአለሁ:: ይህም ቢኾን፡ በእኔ፡ በግሌ በኩል ያለውን ብቻ አስታውሼ የጻፍኩት እንጂ፡ እያንዳንዱ ደግሞ፡ በእየበኩሉ የደረሰበትን፥ ያየውንና የሚያውቀውን ኹሉ፡ ሳይፈራና ይሉኝታ ሳይዘው፥ ወይም ሌላ ጥቅም ሳያታልለው፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ በግልጽ የሚናገርና የሚጽፍ ቢኾንማ ኖሮ፡ የዛሬውም ኾነ የወደፊቶቹ ትውልዶች፡ የቱን ያህል በተጠቀሙ ነበር!? እርግጥ፡ አገር፡ በማናቸውም አግጣጫ፡ እየጸናና እያደገ፥ እያማረም የሚኼደው፡ በግለሰብም ኾነ በሕዝብ ደረጃ፡ ኹሉም፡ በዚህ መልክ፡ ስሕተትንና ጉድለትን፥ ጥፋትንም በመግለጽ፡ ግዳጁን ሲፈጽም እንደኾነ ሊታወቅ ይገባል::

፭ኛ. እኔም፡ በዚህ መጽሐፍ አማካይነት፡ ይህንኑ ግዳጄን ልፈጽም የሞከርኩት፡ የማንንም ስምና መልካም ዝና ለማጉደፍ ብዬ አይደለም:: በመጀመሪያ፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን በሚመለከት፡ ምንም ነገር ለመጻፍ፡ እንዳችም ዕቅድ አልነበረኝም፤ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ እንደሚነበበው፡ ስለእርሳቸው ሰውነትና ምግባር፡ እንዲህ በስፋት እንዳትትና በጥልቀት እንድተች ያስገደደኝ፡ አንድ ታላቅ ምክንያት፡ ከዚያ፡ ከላይ ከተጠቀሰው ራስ ተፈሪያዊ ቀረበልኝ::

ታላቁም ምክንያት፡ ራስ ተፈሪያውያን፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን የአምላክነት መታወቂያ ማኅተም፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ በመስጠት፥ እርሳቸውንም፡ "አምላካችን ናቸው!" በማለት፡ ከመመለክ ደረጃ ሊያደርሷቸው ስለሞከሩ፡ ይህን የተሳሳተ ሙከራቸውን፡ ባጭሩ ለመቅጨትና ሓሳዊ እምነታቸውን ወደእውነተኛው ሃይማኖት በማቃናት፡ ለማስተካከል መኾኑን አበክሬ አስገነዝባለሁ።

መቼም፡ ማነኛውም እውነተኛ ኢትዮጵያዊ እንደሚያምነው፡ ሊመሰገን የሚገባውን የሚያውቅና ዋጋውን የሚከፍል፡ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ስለኾነ፥ እኛም፡ የሚገባንን ከመፈጸም በቀር፥ ከማንም ምስጋናን መጠበቅ፥ ወይም ለማንም ምስጋናን ማቅረብ የሚገባን ስላልኾነ፡ እኔ፡ በዚህ መጽሓፍ ውስጥ፡ የምስጋና ቃልን፡ ለማንም ለማበርከት አልሞከርኩም። በእግዚአብሔር ዘንድ ቀርቶ፡ በሰዎች ዘንድ እንኳ፡ የሚያስመሰግን ሥራ መኖር ያለመኖሩንማ፡ በተሠራው የሰዎች ሥራ ላይ የደረሰው አጠቃላይ ጥፋት፡ ራሱ በቂ ምስክር ኾኖ፡ ይኸው እየተናገረ አይደለምን? ይኹን እንጂ፡ ሰው በሚመለከተው ግብዝነት ሳይኾን፡ እግዚአብሔር ብቻ በሚያውቀው እውነተኛነት፡ ራሳቸውን፡ በሃይማኖትና በምግባር፥ ያም ባይቻላቸው፡ በአማናዊው ንስሓ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከተፈጸመው፡ ክህደት፥ ዓመፅና ምንዝርና፡ ነጻ ያደረጉትን፡ የቤተ ሕዝቡን፥ የቤተ ክህነቱንና የቤተ ምልክናውን አባሎች፡ በግለሰብም ኾነ በኅብረተሰብ ደረጃ፡ በዚህ መጽሓፍ ውስጥ የተሠነዘረው ኃይለ ቃል የማይመለከታቸው መኾኑን፡ አስቀድሜ ልገልጽ እወድዳለሁ።

ቀጥሎ፡ የእርሳቸውን፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴንም ኾነ የሌሎቹን ስም እያነሣሁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ የተፈጸመውን በደል በግልጽ የጻፍኩት፡ ለአጼ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት መፈራረስና ለእነዚያ መቅሠፍቶች ተከታትሎ መድረስ፡ እውነተኛውና ትክክለኛው ምክንያት ምን እንደኾነ፡ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት ዘንድ፡ በገሃድ ታውቆ፥ በትውልዱም ዘንድ፡ ይህ እውቀት፡ እንደመቀጣጫ ትምህርት ኾኖ፡ ለወደፊቱ፡ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ ለማሳሰብ ነው። ቤተ ሕዝቡ፡ በውስጡ፡ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን እንደያዘ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ አገሩ ኢትዮጵያ፡ ያለችበትን እውነተኛ ኹኔታ፡ አንዳችም ነገር ሳይደበቀው፡ በትክክልና በግልጽ እንዲያውቅ ማድረግ እጅግ ያስፈልጋል። ራሱንና የራሱ የኾነውን ኹሉ፡ መጠበቅና ከጠላት ተከላክሎ ማዳን የሚችለው እኮ፡ እንዲህ ሲኾን ብቻ ነው። ይህም፡ በዘወትር ደረጃ መቀጠል አለበት።

፮ኛ. ይህ ዓይነቱ አሠራር፡ ቀደም ብሎ ተለምዶ ቢኾን ኖሮ፡ ማለትም፡ በዚህ ዘመናችን፥ ከዚያም በፊት፡ የኾነውን ኹሉ፡ ትውልዱ፡ በግልጽ እንዲያውቀው ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፡ አገራችንን፡ ዛሬ፡ ደርሶባት ከሚታየው ጥፋትና ውድቀት ማዳን በተቻለ ነበር። ይህም ማለት፡ ለምሳሌ፡ በጉዲት ጊዜ የነበረው ትውልድ፡ ከእርሷ መነሣት በፊት ስለነበረው፡ ስለአገሪቱ አካኼድና ስለመንግሥቱ አመራር፥ ስለሕዝቡም ኹኔታ፡ ክፉውንም ደጉንም፡ በአጠቃላይ፡ እውነተኛውን፡ በግልጽ እንዲያውቀው ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፡ ያን የመሰለ ታላቅ ጥፋት ባልደረሰበት ነበር፤ ከእርሷ በኋላ የመጣው ትውልድም፡ የጉዲትን የጭካኔ ኃይል ያስከተለው ምክንያት ምን እንደነበረ፡ ታሪኩን፡ በግልጽና በትክክል እንዲያውቀው ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፡ የአሕመድ ግራኝን መቅሠፍታዊ ሠይፍ ማስቀረት በቻለ ነበር። ከዚያ ወዲህ እንሠራርቶ፡ ህልውናውን የቀጠለውም ትውልድ፡ ምንም ነገር እንዲያውቅ አልተደረገም።

ማለትም፡ ቀደም ብለው ደርሰው ስለነበሩት፡ ስለጉዲትና ስለአሕመድ ግራኝ የግፍ ድርጊቶች፡ ከነመንሻ ምክንያቶቻቸው፡ ግልጹንና እውነቱን እንዲያውቅ ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፡ ተከታትለው ከደረሱት፡ ከደርቡሾች፥ ከግብፆችና ከቱርኮች፥ በመጨረሻም፡ ከፋሺስት ኢጣልያን ወረራዎችና የእልቂት ጽዋዎች፡ ራሱንም፥ አገሩንም ማዳን በቻለም ነበር።

የዛሬውም ትውልድ፡ ለኢጣልያ ፋሺስትና ከዚያ በፊት ለተካኼዱበት ወረራዎች፡ እውነተኛዎቹና ትክክለኛዎቹ ምክንያቶች ምን እንደነበሩ፡ ከነግብረ አበሮቹ ማንነትና ከነጥፋቶቹ ዓይነት፡ በግልጽ እንዲያውቃቸው ተደርጎ ቢኾን ኖሮ፡ እስካሁን፡ በተለያየ ስምና መልክ እየተካኼደበት፥ ተቀፍዶበትና እየማቀቀ ከሚገኝበት፡ የባዕዳን ረቂቅና ግዙፍ ወረራ፥ የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ቀምበርም ሊድን በቻለ ነበር።

እንግዴህ፡ መልካው ሞልቶ፡ አላሻግር ባለው ወንዝ ዳር ቆሞ፡ ውኃው እንዲጉድልለት፡ በማሲንቆው ሲያወድሰው ለታየው፡ አዝማሪ፡ "ቆሞ የሚሰማህ ከሌለ፡ ምን ያደክምሃል?" እንደተባለው ካልኾነ በስተቀር፡ ይህ ትውልድ፡ ልብ አግኝቶና ሕሊናው ተመልሶ ከኾነ፡ ወደፊት፡ በየዓርባ ዓመቱ፡ ከሚደርስበት ይህን ከመሰለው ጥፋትና ውድቀት ለመዳን ይችል ዘንድ፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በቀረበው መልክ፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ሊያውቀው የሚገባውን ማናቸውንም ድርጊት፡ ገላልጾ የማሳወቁን አሠራር ማስለመዱ፡ እጅግ አስፈላጊ ይኾናል። ከዚህም ጋር፡ ራሷን፡ ኢትዮጵያን፥ ሃይማኖቷንና ሕዝቧን በሚመለከት፡ ከእግዚአብሔር በተሰጠውና ጸንቶ በኖረው ሥርዓተ መንግሥት መሠረት፡ ቤተ ክህነቱንና ቤተ ምልክናውን የሚያስገኘው፡ ቤተ ሕዝቡ፡ ሳያውቀው፥ ሳይመክርበትና ሳይስማማበት፡ አንዳችም የሚሰጥ ውሳኔና የሚፈጸም ተግባር፥ የሚዘረጋም ዕቅድ እንዳይኖር፡ ብርቱ ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚገባ፡ ዓቢይ ጉዳይ ነው።

፯ኛ. የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እውነት እንጂ፡ ሐሰት አይስማማትም። ምክንያቱም፡ እውነት፡ የእግዚአብሔር ስትኾን፡ ሐሰት ደግሞ፡ የዲያብሎስ በመኾኑ ነው። ከላይ እንደተጠቀሰው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለኾነች፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ የዲያብሎስን ሐሰት ስትቃወም ኖራለች! አሁንም ትቃወማለች! ወደፊትም፡ ስትቃወም ትኖራለች። የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷም፡ የተመሠረተችው፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ እንጂ፡ በዲያብሎስ ሐሰት ላይ ስላልኾነ፡ ይኸው፡ የሐሰት አባት፡ ዲያብሎስና ሠራዊቱ፡ እየተከታተሉ፡ በሙሉ ኃይላቸው፡ ሊያጠቋት ቢሞክሩም፡ አትሸነፍም! አትጠፋም። የማትሸነፈውና የማትጠፋው፡ በመጨረሻም፡ "ምእ ኦንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" በሚለው መለኮታዊ ዐርማዋ ምክንያት፡ እኒህን ጠላቶቿን ኹሉ ደምስሳ፡ እርሷ ብቻ፡ በድል አድራጊነትና በሕያው ምስፍና፡ ለዘለዓለም የምትኖረው፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ በመመሥረቷ መኾኑ፡ በኢትዮጵያውያን ወዳጆችም ኾነ ጠላቶች ዘንድ ሊታወቅ ይገባል።

ኢትዮጵያ፡ ከእግዚአብሔር ያገኘችው ኢትዮጵያዊነቷ፡ ማለትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቷ፡ ከነምግባሩዋና ሥርዓቷ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ፍጹም የነጻችና የቀናች ስለኾነች፡ የርኩስ መንፈስ ከኾነው ሐሰትና ባዕድ አምልኮ፥ ማለትም፡ በየግለሰቡ ዘንድ፥ በየቤተሰቡ ውስጥና በየኅብረተሰቡ መካከል፡ በሥውር ሰፍኖ ከሚገኘው፡ ከጨሌ፥ ከጥንቆላ፥ ከጋኔን ጉተታ፥ ከተመሳሳይ የርኩሳን መናፍስትና የጣዖት አምልኮ ልማድ ጨርሳ መጥዳትና ፈጽማ መጥራት አለባት! ይህም፡ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይከናወናል።

እንዲሁም፡ ባዕዳንና የራስ ተወላጆች ሳይቀሩ፡ ለሰብአዊ ዓላማቸው አካኼድና አፈጻጸም ሲሉ፡ ሐሰቱን፡ እውነት እያስመሰሉ፡ ኹን ብለው፡ አላግባብ፡ በሥርዋፅ የጨመሩዋቸውን ሳንከችና ጥፋቶች አስወግዳ፡ በሰዎች የተንኰል ድርጊት የተዛባውንና የተቃወሰውን አቋሟን በማስተካከል፡ ወደጥንታዊው መለኮታዊ መሠረቷ መመለስ አለባት!

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"እኔ፡ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ! ልፈጽም እንጂ፡ ለመሻር አልመጣሁም!"* ብሎ፡ ከኹለት ሺህ ዓመታት በፊት፡ ይህችን ሃይማኖት፡ በራሱ የአዲስ ኪዳን ደም መሥዋዕትነት እንዳጠዳትና እንዳጠራት ኹሉ፡ ዛሬም፡ ይህ የማጥዳቱና የማጥራቱ ተግባር፡ በዚሁ፡ ቅዱስ ሥጋና ደም፡ ከራስና ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ተነሥቶ፡ በቤተሰብ በኩል አልፎ፡ እስከቤተ ሕዝቡ፥ ቤተ ክህነቱና ቤተ ምልክናው ተጠሪዎች፥ ከዚያም፡ ዛሬ፡ በዓፀደ ነፍስ እስከሚገኙት፡ እስከአጼው ድረስ ተካኺዶ መከናወን አለበት:: ያም፡ በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ከግቡ ሊደርስ፡ ይኸው በመንገዝ ላይ ይገኛል::[፯]

በአሁኑ ዘመን፡ ይህ ትውልድ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖቱ ላይ፡ በይፋ በፈጸመው ዓመፅ፥ ክህደትና አመንዝራነት ምክንያት፡ ረድኤተ እግዚአብሔር የተለየው በመኾኑ፡ ከላይ የተጠቀሱት መቅሠፍቶች እየወረዱበት ከመሠቃየቱ ጋር፡ ሐሰት እንደሠለጠነበት፥ የሐሰት አባት ዲያብሎስም እንደነገሠበት፡ እነሆ፡ በገሃድ ይታያል:: ነገር ግን፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አምላክ፡ ከነእናቱ፡ የቤተ ሕዝቡን፥ የቤተ ክህነቱንና የቤተ ምልክናውን፡ የሃይማኖትና የምግባር ታማኝነት ሊፈትን፥ በውጤቱም፡ ኹሉን ታዝቦ፡ ለኹሉም፡ የሚገባውን ዋጋ ሊከፍል፡ ይህን የመከራ መዓቱን ያውርድ እንጂ፡ ዛሬ፡ በኢትዮጵያ የሠለጠነውና የሠፈነው፡ ይህ ኹኔታ ሲቀጥል ይኖራል ማለት አይደለም:: ጊዜያዊ ነው፤ ያልፋል:: በኢትዮጵያ፡ እንደገና ገዝፎ የሚቀጥለውና ለዘለዓለም ጸንቶ የሚኖረው ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የተመሠረተችው፥ *"ምእ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ"* የተባለው፡ ኢትዮጵያዊው ኢየሱስ ክርስቶስና *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር"* የተባለችው፡ ኢትዮጵያዊት እናቱ ድንግል ማርያም፡ በድል አድራጊነት ነግሠው የሚመሩዋት መንግሥት፡ ሥርዓት እንጂ፡ ዛሬ የሚታየውን የመሰለው፡ የባዕዱ አለመኾኑን፡ ያለፈው ያገሪቱ ዜና መዋዕል ስለሚያረጋግጥ፡ ይህን እውነታ መጠራጠር አይቻልም::

እንግዴህ፡ ይህን መጽሐፍ የሚመለከት እውነተኛ ኢትዮጵያዊ፡ በተለይም፡ ወጣቱ፡ ሴቱም፥ ወንዱም፡ የዲያብሎስን ሐሰት፡ በግልጽ እየተቃወመ፡ ለእግዚአብሔር እውነት፡ በይፋ በመቆም፡ እውነተኛ ኢትዮጵያዊነቱን፡ ለራሱም፥ ለፈጣሪውም፥ ለሰውም ማስመስከር አለበት:: *"በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፡ እኔም፡ በአባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔም፡ በአባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ!"* ያለው፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ በምግባር ሲፈጸም፡ ትርጉሙ ይህ ነውና:: ኢትዮጵያዊነትም፡ ሃይማኖት ስለኾነ፡ ይህንኑ ሃይማኖቱን፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ በምድር ላይ፡ ለሰው ልጆች፡ በሚያበረክተው መልካም ምግባር የሚፈጽመው ካልኾነ በቀር፡ ሃይማኖቱ፡ ትርጉምም፥ ዋጋም እንደሌለው፡ በመለኮታዊ ቃል ተነግሮአል::[፰]

ሐሰትን ታቅፎ መኖር፡ ለእውነተኛ ሰው እንዴት ይቻለዋል?

*ታዲያ፡* ከዚህ ከደረሰባት ችግሩዋ ይታደጓት ዘንድ፥ ከዲያብሎስና ከሠራዊቱ ጋር በምታካኺደው፡ የመጨረሻ ታላቅ ሰልፏም ላይ ተጋፍጠው ይታገሉላት ዘንድ፡ የተዘጋጁ፡ እውነተኞችና ታማኞች አርበኞች ልጆቿ፡ አሉላት ወይ? እኒህ ልጆቿ፡ ለግል ስምና ክብር፥ ጥቅምና ምቾት ሳይኾን፡ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እውነት ለመሠዋት፡ ያለአንዳች ውልውልና ጥርጥር፡ በቆራጥ፡ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ይጋደሉላት ዘንድ፡ ይህን፡ የዘመቻ ጥሪዋን ተቀብለው፡ ከቤተ ሕዝቧም፥ ከቤተ ክህነቷም፥ ከቤተ ምልክናዋም መካከል፡ ብቅ ብቅ እንዲሉላት ትፈልጋለች! ትጠብቃለችም!

ይህን ጥሪዋን ለመቀበል፡ ፈቃደኞች ለሚኾኑት፡ ይህን እላለሁ፡- *"ፍጹም ፍቅር፡ ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ፡ በፍቅር ፍርሃት የለም! ፍርሃት ቅጣት አለውና! የሚፈራም ሰው፡ ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።"* የሚለውን የመንፈስ ቅዱስ ቃል በመከተል፡ እናታችንን ኢትዮጵያን፡ በእውነት የምትወድዷት ከኾነ፥ እርሷን መውደድ ማለት ደግሞ፡ እግዚአብሔርን መውደድ ስለኾነ፡ ስለእርሷ ስትሉ፡ ሥጋዊ ጥቅማችሁን ብቻ ሳይኾን፡ ራሱን ሕይወተ ሥጋችሁን ሳይቀር፡ ያለፍርሃትና በፍጹም ቆራጥነት፡ መሥዋዕት ለማድረግ ተዘጋጅታችሁ የቀረባችሁ መኾናችሁን፡ አስቀድማችሁ፡ ለየራሳችሁና ለእግዚአብሔር፥ ለሰውም ማረጋገጥ ይኖርባችኋል። ይህም ማለት፡ ይህ መጽሐፍ፡ ስለኢትዮጵያና ስለኢትዮጵያዊነታችሁ፡ የእግዚአብሔር እውነት የሰጠችውን የምስክርነት ቃል የያዘ ስለኾነ፡ እርሱን አንሥታችሁና ገላልጣችሁ ለማንበብ አትፍሩ! ከፈራችሁ፡ የእግዚአብሔር እውነት የኾነችውን ኢትዮጵያን፡ አትወድዷትም! ካልወደዳችኋት፡ አትፈልጓትም! ካልፈለጋችኋት፡ የእርሷ ልጆች አይደላችሁም! እርሷ፡ በእግዚአብሔር እውነትነቷ፡ ኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም ኾና ስለተገለጸች፡ የእርሷ ወገን፥ የእርሷ አገልጋይ አይደላችሁም ማለት ነው! እንዲህ ካልኾናችሁ ደግሞ፡ ይህ አቋማችሁ፡ የሐሰት፥ ያውም የዲያብሎስ ወገኖችና አገልጋዮች ያደርጋችኋል።

በመጨረሻ፡ ሳልገልጽ የማላልፈው አንድ ነገር አለ። ከዚህ በፊት በታተሙትና በዚህኛው መጻሕፍቶቼ ውስጥ በሠፈሩት መልእክቶችና በሠነዘርኳቸው የእውነት ኃይለ ቃላት ምክንያት፡ ምን እንደምባል፥ ምን ዓይነት የተለያየ ስም እንደሚወጣልኝም፥ በእኔና በቤተሰቤ ላይ፡ ሊፈጠር ስለሚችለው የተቃርኖ አስተያየት ጭምር፡ ኹሉንም፡ እስካሁን ባየሁትና በተረዳሁት መጠን፡ ወደፊትም፡ ሊደርስ የሚችለውን አውቀዋለሁ። ከላይ እንደገለጽሁት፡ እኔ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ እንደመኾኔ፡ የእኔ ተልእኮ፡ ቀድሞም ኾነ ዛሬ፡ በማናቸውም አስተዳደርና አገዛዝ፡ ስለእርሷ እውነት መመስከር ነው። በዚህ ረገድ፡ ከልጅነቴ ጀምሮ የደረሱብኝ ችግሮች፡ በሚቀጥሉት ገጾች ላይ፡ ተዘርዝረው ቀርበዋል። ለአንድ ሰው ደግሞ፡ በዚህ ዓለም፡ በሰዎች መካከል፡ ስለእግዚአብሔር እውነት መመስከር ማለት፡ "መጠላትና መገለል" መኾኑን፡ የእውነት ሰዎች ኹሉ አስቀድመው ያውቁታል፤ እኔም አውቀዋለሁ። ይህንኑም፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ *"ወንድሞቹ ስንኳ አላመኑበትም ነበርና፡ 'ዓለም፡ እናንተን ሊጠላ አይቻለውም፤ እኔ ግን፡ ሥራው ክፉ መኾኑን እመሰክርበታለሁና፡ እኔን ይጠላኛል"*፥ ለደቀ መዛሙርቱም፡ *"ዓለም ቢጠላችሁ፡ ከእናንተ በፊት እኔን እንደጠላኝ እወቁ! እኔን አሳድደውኝ እንደኾኑ፡ እናንተን ደግሞ ያሳድዷችኋል!"* ሲል በተናገረው መሪ ቃሉ፡ አብራርቶ ገልጾታል።

ስለዚህ፡ እኔም፡ ይህን አውቄ የገባሁበት ተልእኮ ስለኾነ፡ በሰዎች[፲] ዘንድ መጠላቱና ከእነርሱ መገለሉ፡ ለእኔ እንግዳ ነገር ሊኾን አይችልም።

*"እግዚአብሔር ሐወጸ እምሰማይ፡ ላዕለ እጓለ እመሕያው፥ ከመ ይርአይ፡ እመቦ ጠቢብ፡ ዘየኀሥሦ ለእግዚአብሔር። ኵሉ ዐረየ! ወኅቡረ ዐለወ!"*፡ ማለትም፡ *"እርሱን የሚፈልገው አስተዋይ ሰው ይኖር እንደኾነ ሊያይ፡ እግዚአብሔር፡ ከሰማይ ወደምድር እየተመለከተ፡ በሰው ልጆች መካከል ጐበኘ! ነገር ግን፡ ኹሉም፡ በዐመፅ ሥራ አንድ ኾነውና በመተባበር ዓምፀውበት አገኛቸው!"* በሚለው የመንፈስ ቅዱስ ቃል መሠረት፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ ወገን የኾነው ኹሉ፡ የዐመፅ፥ የክህደትና የሐሰት ተገዢና አገልጋይ በኾነበት[፲፩] ጊዜ፡ ታዲያ፥ ስለ"እግዚአብሔር እውነት" ማን ይናገር? ማን ይቁም?

እንደጥንቱ ጊዜ፡ ያ፡ እግዚአብሔር፡ ያውም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ኾኖና በመስቀል ላይ ተዘርግቶ፡ ዛሬ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ *"ወደ ቃል ኪዳን ሕዝቤ፡ ማንን ልላክ? ማንስ፡ 'እሺ ብሎ' ይኼድልናል?"* እያለ በሚጣራበት፡ በዚህ ዘመን፡ እንደማነኛውም ኢትዮጵያዊ፡ ለእኔም፡ በዚህ ተልእኮ ለተጠመድሁት ኢትዮጵያዊ፡ የቀረበልኝ፡ ፈታኙ ጥያቄ፡ ይኼ ኾኖ አገኘሁት! እኔም፡ "ጌታ ሆይ! እነሆኝ፡ እኔ አለሁ!" ብዬ መልስ ሰጥቼ፡ ምንም እንኳ፡ *"እግዚአብሔርም፡ 'ኺድ! ይህን ሕዝብ፡ "መስማትን ትሰማላችሁ፥ አታስተውሉምም፤ ማየትንም ታያላችሁ፥ አትመለከቱምም፤" በላቸው! በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳይፈወሱ፡ የዚህን ሕዝብ ልብ አደንድን! ጆሮአቸውንም አደንቍር! ዓይናቸውንም ጨፍን!' አለኝ"* የሚለው፡ የነቢዩ ቃል፡ ዛሬም እንደጸና ኾኖ ቢታይም፡ ይኸው፡ የበኵሌን ተልእኮ[፲፪] ለማድረስ፡ ይህን መጽሐፍ በማበርከት፡ በአገልግሎቱ ሩጫ ላይ እገኛለሁ።

ተልእኮዬ ምን እንደኾነ፥ በመጨረሻም፡ ከምን እንደሚያደርሰኝ ያወቅሁት፡ ዛሬ ሳይኾን፡ ገና በመጀመሪያ፡ ቃል ኪዳኑን በተቀበልሁባት ዕለት ነበረ። ምክንያቱም፡ የኢትዮጵያዊነቴ ቃል ኪዳን፡ በተለይ ሥልጣነ ክህነትን ስቀበል፡ በበለጠ ተጠናክሮ ነበርና። የቃል ኪዳኑ ተጣማጄ ከኾነችው፡ ከባለቤቴ፡ ከወይዘሮ ራሔል ዘካርያስ ጋር፡ ይህን፡ የተልእኮ ግዳጃችንን ከግብ ለማድረስ ደግሞ፡ *"ማንም፡ ወደእኔ የሚመጣ ቢኖር፡ አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንም፥ ልጆቹንም፥ ወንድሞቹንም፥ እኅቶቹንም፥ የራሱንም ሕይወት ስንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ መስቀሉንም ተሸክሞ፡ በኋላዬ ባይመጣ፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም!"* የሚለውን የጌታ ቃል፡ ኹለታችንም፡ አስቀድመን አውቀነውና ተዘጋጅተንበት ስለነበረ፡ ይኸው፡[፲፫] ጽዋውን በአኰቴት እየተቀበልን፡ ከፍጻሜ ልናደርሰው እንጋደላለን።

አዎን! በተለይ በዚህ የመጨረሻ ዘመን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ ኾኖ መገኘት፥ ማለትም፡ በእግዚአብሔር አምኖና እርሱን እያመለኩ፥ የእርሱን እውነት፥ ሕጉንና ቃሉንም ተከትሎ፡ በእርሱ ሕይወት መኖር፡ እንዴት አስጨናቂና መራራ፥ ከባድም እንደኾነ፡ ይኸው እየነው! ይኹን እንጂ፡ *"በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ! እላችኋለሁና፡ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ፤ አይችሉምም! ...በዓለም ሥላችሁ፡ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን፡ አይዟችሁ! እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ!"* ያለው የጌታችን[፲፬]፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል፡ እያጽናናን፡ በፋናው መሪነት እነሆ እንጓዛለን።

## የፈላስፋው ዝክረ ነገር።

በአሁኑ ጊዜ፡ ከዚህ ደረጃ በደረሰው፡ በዚህ የተልእኮ ጉዟችን መካከል የገጠመንና በብርቱ ትዝ የሚለኝ አንድ ወግ አለ። አግባብነት ያለው መስሎ ስለታየኝ፡ እዚህ ላይ አወሳዋለሁ። በ፲፱፻፰ ዓ.ም. የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድና የአውራጃዋ አስተዳዳሪ ኾኜ፡ ለአገልግሎት ወደአኵስም ስላክ፡ ቋሚና የወደፊት ሥራዬን ከመጀመሬ በፊት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾኑትን፡ የአኵስም ጽዮንን ማኅበር ሹማምንት፡ ማለትም፡ የቤተ ሕዝቡን ሽማግሌዎች፥ የቤተ ምልክናውን አባሎችና የቤተ ክህነቱን ሊቃውንት፡ በጉባኤ ሰብስቤ፡ "እንደምታዩኝ፡ እኔ፡ በዕድሜዬ ታናሽ የኾንሁ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋይ (ካህን) ነኝ፤ እንዲህ እንደመኾኔ፡ በእግዚአብሔር እውነት እየተመራሁ የማካኺደውን ተግባሬን፡ በትክክል ለመፈጸም እችል ዘንድ፡ እኔ ከማውቀው ጋር፡ እስካሁን ጸንቶ እየተሠራበት ያለውን ሥርዓት ብትገልጹልኝ ይረዳኛል!" አልኋቸው።

እስከዚያን ጊዜ ድረስ፡ በቃል ብቻ ይሠራበት የነበረው፡ ያ ሥርዓት፡ በጥያቄዬ መሠረት ተጽፎ፥ የኹሉም ጽሑፍ ኪዳን (Firma ፊርማ) ሠፍሮበት፡ ለአጼው፥ ለእጨጌውና ለሚመለከታቸው ኹሉ ተላልፎ፡ ሥርዓቱ ከጸደቀ በኋላ፡ ስንሠራበት ሣለ፡ ጥንታዊው ሥርዓት፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ በትክክል እንዲሠራበት መደረጉ፡ የግል ጥቅማቸውን ያቃወሰባቸው፥ እንዲሁም፡ ለአኵስም የውኃ ግድብ መሥሪያ ተብሎ የተሰበሰበው የሕዝብ ገንዘብ፡ በዚያው በአውራጃው ይቆይ ዘንድ፡ ሕዝቡ ራሱ እንዲወስን ማድረጌ ያላስደሰታቸው ጥቂት ወገኖች፡ በክፉ መንፈስ፡ በእኔ ላይ መነሣሣት ጀመሩ። ዳሩ ግን፡ ያ፡ ቋሚ ሥርዓትና ውሳኔ እንዲፈርስና ወደቀድሞው አሠራር እንዲመለስ የሚያደርጉት ሙከራና ጥረት የማይሳካላቸው መኾኑን ሲያውቁ፡ እኒያ ወገኖች፡ በሌላው ሥውር ተንኰልና ግልጽ ተቃውሞ ከመጠቀማቸው በፊት፡ በታወቁ የካህናቱ አዛውንቶች አማካይነት፡ መልእክታቸው፡ እንዲህ በሚለው ወግ፡ ወደእኔ እንዲደርስ አደረጉ!

"በአንድ ዘመን፡ አንድ ንጉሥ ነበር። ለእርሱም፡ አንድ ፈላስፋ፡ ማለትም፡ በአእምሮው፡ ብልህ የኾነና ጥልቅ መንፈሳዊ አስተሳሰብ ያለው ወዳጅ ነበረው። ከዕለታት አንድ ቀን፡ ይህ ፈላስፋ፡ "የምነግርህ ትልቅ ጉዳይ አለኝና፡ እንገናኝ!" ሲል ወደንጉሡ ላከበት። ንጉሡም ሲመጣለት፡ "ወደፊት፡ 'እንዲህ እንዲህ' በሚባለው ዓመት ላይ የሚዘንበው የዝናም ውኃ፡ የተለየ ባሕርይ ስለሚኖረው፡ ከእርሱ የሚጠጣ ኹሉ ያብዳልና፡ ማለትም፡ አስተሳሰቡ ይለወጣልና፡ ከአሁኑ፡ የሚያስፈልገውን ዝግጅት ማድረግ እንድትጀምር፡ ሊመጣ ስላለው መከራ፡ አስቀድሜ ልንገርህ ብዬ ነው የፈለግሁህ!" አለው።

"ንጉሡም፡ "ታዲያ፥ ምን ይበጀኛል? ምንስ ላድርግ?" አለው።

"ፈላስፋው ወዳጁም፡- "ሰምተህ የምትፈጽመው ከኾነ፡ እኔ የምሰጥህ ምክር ይህ ነው!" አለው። "አንተና ቤተሰብህ፡ በቤተ መንግሥትህ፥ ሕዝብህ ደግሞ፡ ቢቻል በነፍስ ወከፍ፡ በየወጀዱ (በየአጥር ግቢው)፥ ይህ ባይቻለው ግን፡ በኅብረት እየኾነ፡ በየሠፈሩ፡ ጥልቅና ሰፋፊ ጉድጓድ እየቆፈረ፡ ያ፡ ክፉ ዓመት እስኪመጣ ድረስ፡ ለአንድ ዓመት የሚበቃውን የመጠጥ ውኃ፡ በየዓመቱ ከሚዘንበው ዝናምና ምንጭ ያከማች! የክፉውን ዓመት የዝናም ውኃ ጠጥቶ እንዳያብድ፡ ይህን ምክሬን እንዲፈጽም፡ ለሕዝብህ በጥብቅ አስጠንቅቀህ አውጅ! አንተም፡ ለራስህ፡ ይህንኑ አድርግ!"

"ንጉሡም፡ ለጊዜው ነገሩ ቢያስደነግጠውም፡ መፍትሔውን ጭምር ስለነገረው፡ ወዳጁን አመስግኖ ተሰነባበቱ።

"ንጉሡ ወደቤተ መንግሥቱ እንደተመለሰ፡ የፈላስፋ ወዳጁን ምክር በመከተል፡ በጉዳዩ ላይ፡ ከአማካሪዎቹ ጋር ከተመካከረ በኋላ፡ ነገሩን ለሕዝቡ፡ በአዋጅ አሳወቀ! አዋጁ እንዲፈጸምም ተገቢውን ትእዛዝ፡ ለሹማምንቱ አስተላለፈ። ትእዛዙም፡ በቅድሚያ በራሱ ቤተ መንግሥት ውስጥ፡ በተግባር ላይ እንዲውል አደረገ። ጻሩ ግን፡ ሕዝቡ፡ በኖኅ ዘመን ከደረሰው የጥፋት ውኃ በፊት እንደታየው፡ የሰዎች የቸልተኛነት ድርጊት፡ "ጊዜው ገና ነው! ይቆይ! በሚመጣው ዓመት አደርገዋለሁ!" እያለ፡ ምንም ዓይነት ዝግጅት ሳያደርግ፡ ያ ክፉ ዓመት ደረሰ! ንጉሡ፡ የወዳጁን ምክር ተከትሎ፡ ያከማቸውን የመልካሙን ዘመን ደህና ውኃ፡ ከነቤተሰቡ እየጠጣ፡ አእምሮው ሳይነካ፡ በነበረበት የቀድሞው ኹኔታው ሲቀጥል፡ ሕዝቡ ግን፡ በንጉሡ አዋጅ መሠረት፡ ያዘጋጀው የደህናው ዘመን ውኃ ስለሌለው፡ የተፈራውን የክፉውን ዓመት ዝናም ውኃ እየጠጣ፡ የኖረበት፡ ትክክለኛ እምነቱና ምግባሩ ኹሉ፡ ፈጽሞ ተለውጦ ተገኘ!

"በዚህ ጊዜ፡ ንጉሡና ሕዝቡ፡ በእምነት አስተሳሰባቸውና በምግባር አካኼዳቸው፡ ፈጽመው ስለተለያዩ፡ መግባባት አቃታቸው። በአንድ ወገን፡ ሕዝቡ፡ "ንጉሣችን አበደ! ምን ይሻላል?" ይሉ ጀመር፤ በሌላው ወገን ደግሞ፡ ንጉሡ፡ ያ፡ ለሕዝቡ በአዋጅ የሰጠው፡ የመልካሞቹን ዓመታት የዝናም ውኃ የማጠራቀሙ ትእዛዝ ሳይፈጸም መቅረቱን ባለማወቅ፡ "ሕዝቤ አብዷል! ለእኔ ያለው አስተያየት፡ እንደቀድሞው አይደለም! ምን ኾነብኝ? ጨርሶ መለወጡን ይኸው እመለከታለሁ!" እያለ ይጨነቅ ጀመር።

"ይህን የመሰለ ችግር ሲገጥመው፡ ትዝ የሚለው፡ ያ፡ ፈላስፋ ወዳጁ ስለኾነ፡ ወደእርሱ ኼዶ፡ በራሱና በሕዝቡ መካከል የተፈጠረውን የአለመግባባት ችግር አብራርቶ አጫወተው።

"ፈላስፋውም፡ "እህ!" ብሎ፡ አቀርቅሮ፡ ለጥቂት አፍታ በትካዜ ከቆየ በኋላ፡ ቀና አለና፡ ንጉሡን፡ በተሸበረ ዓይን እያየ፡ "ታዲያ! የዚህን ዓመት ክፉ ውኃ የጠጣችሁ፡ ማነኛችሁ ናችሁ? አንተ ነህ? ወይስ ሕዝብህ?" ሲል በኀዘኔታ ድምፅ ጠየቀው።

"ንጉሡም፡ "እኔማ፡ እንደመከርኸኝ፡ ከነቤተሰቤ እየጠጣሁ ያለሁት፡ በመልካሙ ዘመን ያከማቸሁትን ደህና ውኃ ነው!" ብሎ መለሰለት።

""ሕዝብህስ?" ሲል፡ ፈላስፋው መልሶ ጠየቀው።

"ንጉሡ፡ እርግጠኛውን መልስ ለመስጠት ተቸግሮና ግራ ገብቶት ወዲያ ወዲህ ሲገላመጥ ሳለ፡ ሕዝቡ፡ አዋጁን አክብሮ ያልፈጸመ መኾኑን ተከታትሎ የደረሰበትና በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የተከማቸውን ደህና ውኃ እየጠጣ የቆየ ባለሟል አገልጋዩ፡ ይህን የሚያወቀውን ምሥጢር ለንጉሡ፡ በጆሮው ነገረው። ንጉሡም፡ ይህንኑ መርዶ፡ ለፈላስፋ ወዳጁ አሰማው! አከታትሎም፡ በኀዘንና በትካዜ፡ "ታዲያ፥ ምን ይበጃል? ለዚህስ ችግር፡ ምን የምትሰጠኝ ምክር አለ?" አለው።

"ያም ፈላስፋ፡ እንደንጉሡ፡ በኀዘንና በትካዜ ተውጦ፡ "እንግዴህማ፡ ለዚህ፡ ጽኑ ያገር ችግር፡ ሌላ ምን መድኃኒት ይኖረዋል? መፍትሔ አንድ ብቻ ነው! እርሱም፡ ሕዝብህ፡ አሁን እየጠጡ ያሉትን፡ የዚህን፡ የክፉውን ዓመት ውኃ፡ አንተም፡ ጠጥተህ እንደእነርሱ ማበድ!!!" ሲል፡ የመጨረሻውን ምላሽ፡ ለንጉሡ ሰጠው።

"ንጉሡም፡ በእምነቱ አቋም እንደጸና፡ ሥልጣኑን በመልቀቅ ፈንታ፡ ከዚያ ይልቅ፡ ለችግሩ መፍትሔ፡ የወዳጁን የፍልስፍና ምክር፡ እንደወትሮው መቀበልን መርጦ፡ ሕዝቡ እየጠጣ ያለውን፡ የዘመኑን ውኃ ጠጣ! በዚህ ጊዜ፡ ሕዝቡ፡ "አብዶ የነበረው ንጉሣችን፡ ደህና ኾነልን!" ብለው፡ ታላቅ የደስታ በዓል አድርገው፡ ኹሉም በስምምነት ኑሮአቸውን ቀጠሉ::" "ብጤ ከብጤው" የሚለውን ፈሊጥ፡ ፍጹም ተግባራዊ አደረጉት!

እንግዲህ፡ እኒያ፡ በእኔ ላይ፡ በክፉ መንፈስ ተነሣሥተው የነበሩት ጥቂት ወገኖች፡ በካህናቱ አዛውንት አማካይነት፡ ወደእኔ ያስተላለፉትን የማስጠንቀቂያ መልእክት የያዘው፡ ታሪካዊ ወግ፡ ይህ ነበር! ያም መልእክት፡ በበላዮች የጸደቀው "'ጥንታዊው፥ አማናዊውና ቋሚው፡ ሥርዓት ይህ ነው' እያልህ፡ በግትርነት የተከተልከውን የአሠራር መንገድ ሻረውና፡ የቅርቦቹ ንቡራነ እድ፡ በጊዜያችን ያደርጉ እንደነበረው፡ ከእኛ ጋር ተስማምተህ፥ እኛ የምንልህንም ቃል እየፈጸምህ ኑር! እንዲህ ካልኾነ፡ እዚህ መቆየት አለመቻልህን እወቀው!" የሚል ነበር::

የጌታዬ የኢየሱስ ክርስቶስ እናቱ፡ አማናዊቷ ታቦተ ጽዮን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከአገልጋዮቿ፡ ከባለቤቴና ከእኔ፡ በእርግጥ ስላልተለየች፡ ያ፡ የአዛውንቱ ወግ፡ በእኛ ላይ ሳይሠራ ቀረ! በሥራዬ ላይ፡ በክፉ መንፈስ ተነሣሥተው የነበሩት ጥቂት ወገኖች የጠጡትን፡ ያን ውኃ፡ እኔ፡ "አልጠጣም!" አልሁ፤ ማለትም፡ "የኢትዮጵያ ሃይማኖታዊ ሥርዓት፡ በባዕዳን የፍልስፍና ወግ አይሻርም!" ብዬ፡ በጥንታዊው ሥርዓት የጀመርኩትን ሥራዬን፡ በእግዚአብሔር እውነት እየተመራሁ፡ ለብሔራዊው የቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጃጅነት አገልግሎት እስከተጠራሁበት ጊዜ ድረስ፡ በዚያው፡ በአኰስም ቀጠልሁ::

በዚህ ጊዜ፡ እኒያ፡ የግል ጥቅማቸው የታገደባቸውና ሰብአዊ ዓላማቸው የተቃወሰባቸው ጥቂት ወገኖች፡ ተቃውሟቸውን በይፋ፥ ከዚያም፡ በኃይል ማካኼድ ጀመሩ:: ያም፡ የማይሳካላቸው ቢኾን፡ አቤቱታቸውን ለአጼው አቅርበው፡ ጉዳዩ፡ በከፍተኛ ደረጃ፡ በዳኝነት እንዲታይ ተወሰኖ፡ የፍትሑ ፈጻሚ፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ፡ በአኰስም የተከናወነውንና እንዲታወቅ ያልፈለግሁትን፡ የእኔን የሥራ ፍሬ፡ በበለጠ በማሳወቅ፡ በእግዚአብሔር እውነት አሸናፊነት አበቃ!

በ፲፱፻፷፫ ዓ.ም. የዑጋንዳ ሕዝብ፡ ብሔራዊ፥ መንግሥታዊና ሃይማኖታዊ በዓሉን ባከበረበት፥ ታላቅ ጉባዔንም ባደረገበት ጊዜ፡ በክብር እንግድነት፡ አጼ ኃይለ ሥላሴን ጋብዞ፡ ሊገኙለት ባለመቻላቸው፡ እርሳቸውንና የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ ኢትዮጵያን፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ምልክናዋንና ቤተ ክህነቷን በአንድነት ወክዬ መገኘት የምችል፡ በአኰስም ንቡረ እድነቴ፡ እኔ ብቻ በመኾኔ፡ ለዚያ እንደራሴነት ተልኬ እንደነበረ፡ እዚህ ላይ ሊወሳ ይገባል:: ከዚያ ተልእኮዬ ስመለስ፡ ለጉዞው ተመድቦ፡ ከመንግሥት ከተሰጠኝ የኪስ ገንዘብ ላይ ወጪ አድርጌ የተረፈኝን፡ በመለስኩበት ጊዜ፡ ድርጊቱ ያልተለመደ በመኾኑ፡ የጽሕፈትና የገንዘብ ምልክናዎች ሹማምንት፡ ሒሳቡን፡ በምን ርእስና መልክ ተመላሽ ሊያደርጉት ተቸግረው እንደነበረ፥ ይህን የመሰለው ኹኔታም፡ በቤተ ክህነትም ሣለሁ እየደረሰ፡ የሒሳብ ችግር ይፈጥር እንደነበረ ትዝ ይለኛል::

ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗ የሚረጋገጥበት፡ ያ፡ የአኰሱሙ ሥርዓት፡ በአሁኑ ዘመን፡ የደረሰው፡ አጠቃላይ የዓመፅና የክህደት ኃጢአት ባስከተለው የቅጣት መቅሠፍት ምክንያት፡ ለጊዜው የተሻረ መስሎ ይታይ ይኾናል::

ይኹን እንጂ፡ ይኸው ሥርዓት፡ ወደፊት ተመልሶ፡ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይኾን፡ በመላው ዓለም፡ በይፋ እስኪሠፍን ድረስ፡ ህልውናው፡ በዚህ በአንዱ ኢትዮጵያዊ፡ ወይም እርሱን በመሰሉት በሌሎቹ ጥቂቶች እውነተኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሰውነት፡ ሕያው ኾኖ፡ በምድር ላይ፡ ለዘለዓለም ይቀጥላል። ይህም ማለት፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት መኾኗን፡ ዓለሙ በሙሉ፡ በዓመፅ ክዶ ቢተወው እንኳ፡ እኔ፡ አንድ ኢትዮጵያዊ ብቻ ካመንኩባት፡ ህልውናዋ፡ በምድር ላይ ሕያው ኾኖ ይቀጥላል ማለት ነው።

እኔን በሚመለከት፡ ይህና ሌሎቹ፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተወሱት፡ ተመሳሳይና ተከታታይ ኹኔታዎች፥ እንዲሁም፡ እስከዛሬ እየቀጠለ ያለው፡ መንፈሳዊው ሰልፍና ተጋድሎ፡ እዚህ ላይ ለንባብ መቅረባቸው፡ የግል ሙያን ወይም የሥራ ፍሬን፡ በዝና መልክ ለመግለጥ ሳይኾን፡ ስለእግዚአብሔር እውነት ለሚቆሙና ለሚሠሩ ኹሉ፡ የሚያበረታታ መንፈስን የሚያስገኝ ምንጭ ይኾናል ብዬ ተስፋ ስላደረግሁ ብቻ መኾኑን እንደገና ልገልጽ እወድዳለሁ።

## የ"እብደት" ትርጉም፡ እንደተመልካቹ አቋም ነው።

ከላይ የተነገረው የአዛውንቱ ወግ፡ ዛሬም፡ ለእኔና እኔን ለመሰሉት ኹሉ፡ ፈተና ኾኖ የመቅረቡ ነገር፡ መቀጠሉ እንደማይቀር ይታወቃል። የዚህም ምክንያት፡ "እግዚአብሔር የለም" እስከሚል ደረጃ የደረሰውንና ጊዜ ያመጣውን፡ የሐሳውያንን ሰይጣናዊ ዓላማ ባለመቀበል፡ ጥንት፡ ከመነሻው ጀምሮ የኖረውን፡ እውነተኛውን፡ የኢትዮጵያ የቃል ኪዳን ሃይማኖትና ሥርዓት ጠብቆ መገኘቱ፥ በዚያውም ጸንቶ መቀጠሉ፡ አንድን ኢትዮጵያዊ/ት፡ ከኅብረተሰቡ የሚለየው ከኾነ፡ በእርግጥ፡ "ስምንተኛው ሺ" ከሚባለው፡ የዓመፅ፥ የክህደትና የአመንዝራነት ዘመን ውስጥ እየኖርን መኾናችንን፡ ሌላው ባያምንም፡ ቢያንስ፡ ቢያንስ፡ ለየራሳችን እያረጋገጥን እንመሰክራለን።

አዎን! የሰው ልጆች፡ በእግዚአብሔር እውነት ላይ ሊቆም የሚገባው ኹለንተናዊ አቋማቸው፡ ቀውስ ሲኖርበት፡ ማለትም፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ውስጣቸው በሚኖራቸው፡ የእምነት አስተሳሰባቸውና በውጭ በሚያሳዩት፡ የምግባር አካኼዳቸው፡ ከዚያች፡ ከእግዚአብሔር እውነት የተለዩ ኾነው ሲገኙ፡ ያን ጊዜ፡ በአቋሙ የጸናው ሰው፡ ከአቋማቸው የተነዋወጹትን፡ "ንስሓ ግቡ!" ሲል፥ እነዚህ፡ ከአቋማቸው የተነዋወጹት ደግሞ፡ ያን፡ በአቋሙ የጸናውን፡ "አበደ!" ይሉታል።

ሰዎች፡ በእግዚአብሔር ስም ሳይቀር በመጠቀም፡ ለራሳቸው ተስማምቷቸውና ተመችቷቸው ይኖሩበት ዘንድ ካቋቋሙት ሥርዓት ጋር፡ ዲያብሎስ፡ የራሱን ክፉ መንግሥት አቀናጅቶና የሥልጣን አውታሩን ተብትቦ፡ የአገዛዝ ቀምበሩን ባጠናከረበት ኅብረተሰብ መካከል፡ በእግዚአብሔር እውነት መኖር፡ አዎን፡ "እብድ!" ማሰኘቱ፡ ከቶ፡ እንግዳ ነገር ሊኾን አይችልም። በዚህ ዓለም፡ ለምናሳልፈው ሕይወተ ሥጋ፡ ፍጹም አርአያችን አድርገን በምንመለከተውና በምንከተለው፡ በራሱ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የደረሰው፡ ከዚህ የባሰውና የከፋው፡ የሰዎች፡ የምጸት (የማላገጥ) አስተያየት፥ አነጋገርና አደራረግ፡ እያስረዳ ያጽናናናልና!

ይኸውም፡ እንዲህ በሚለው የወንጌል ቃል ተረጋግጦ ይታወቃል፡፡ ሰው የኾነው አምላክ፡ እርሱም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በምኵራብ፥ በከተማና በየገጠሩ፥ በየሜዳውና በባሕር ላይ ሳይቀር፡ በመዘዋወር፡ ሕሙማንን እየፈወሰ፥ ስለእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለሕዝቡ ሲያስተምርና ሲሰብክ ውሎ፡ በፊቱ እየተደፉና *"አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ!"* እያሉ የሚጮሁትንም ርኩሳን መናፍስት፡ ከሰዎች እያስወጣ፡ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደበዓቱ በሚመለስበት ጊዜ፡ *"እህል መቅመስ እንኳ እስኪሳናቸው ድረስ፡ ብዙ ሕዝብ፡ እንደገና ተሰበሰቡ፡፡ ዘመዶቹም ሰምተው፡ 'አበደ!' ብለዋልና፡ ሊይዙት መጡ፡፡ ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም፡ 'ብዔል ዜቡል አለበት!' ደግሞም፡ 'በአጋንንት አለቃ፡ አጋንንትን ያወጣል!' ብለው ተናገሩ፡፡"* እንዲሁም፡ ጌታችን ኢየሱስ ከተናገረው *"ቃል የተነሣ፡ በአይሁድ መካከል፡ እንደገና መለያየት ኾነ! ከእነርሱም ብዙዎች፡ 'ጋኔን አለበት፤ አብዷልም፤ ስለምን ትሰሙታላችሁ?' አሉ፡፡"*[፲፩] በሚለው የወንጌል ቃል፡ ይህ እውነታ፡ በሚበቃ ተገልጾ በመጻፉ ነው፡፡

በኅብረተሰቡ ዘንድ፡ ይህ፡ "አበደ!" የሚለው ስም የተሰጠው፡ ለሰባቱ ኪዳናት ሰባተኛና መደምደሚያ፥ የመጨረሻ ማኅተምና ዘውድ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ አይደለም፤ ከእርሱ በፊትና ከእርሱ በኋላ፡ የእርሱን ፈለግ ለተከተሉት ኹሉ ጭምር እንደነበረ ይታወቃል፡፡ ከእነዚህ መካከል፡ "ቅዱሱን ኪዳን እንጠብቃለን!" ብለው፡ በእግዚአብሔር ላይ ባላቸው ሃይማኖታቸውና አምልኳቸው ጸንተው በመገኘታቸው፡ ከአዳምና ሔዋን ወዲህ፡ በዘመናቸው በነበረው ኅብረተሰብ ዘንድ እየተዘበቱባቸውና እየተፌዘባቸው የተገለሉትን፡ በብሉዩ ዘመን፡ ኖኅንና ቤተሰቡን፥ መልከ ጼዴቅንና ወገኖቹን፥ አብርሃምንና ቤተሰቡን፥ ሙሴንና ቤተሰቡን፥ ዳዊትንና ቤተሰቡን፥ በዘመነ ሐዲሱም፡ ከራሳቸው ከሐዋርያት ጀምሮ፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውና አምልኳቸው፡ ራሳቸውን መሥዋዕት እያደረጉ፡ በሰማዕትነት ያለፉትን፡ ጻድቃንን፥ ባሕታውያንንና ገዳማውያንን በምስክርነት መጥቀስ ይበቃል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ፡ በልጅነቴ የኾነ አንድ ሌላ ነገር፡ በዚህ አጋጣሚ፡ አሁን ትዝ ስላለኝ፡ እዚህ ላይ ልጠቅሰው እወድዳለሁ፡፡ በ፲፱፻፵፯ ዓ.ም.፡ ማለትም ገና የ፲፯ ዓመት ወጣት ሳለሁ፡ በቤተሰብ ናፍቆት ምክንያት፡ ከአንድ ዓመት በላይ ልቆይበት ወዳልቻልኩት ሐረር፡ መምህራን ማሠልጠኛ ትምህርት ቤት፡ በአዳሪ ተማሪነት ኼጄ ነበር፡፡ የትምህርቱ ገበታ እንደተጀመረ ወዲያው፡ ከዕለታት በአንዱ ቀን፡ ጠዋት፡ በመኝታ ክፍላችን፡ ከእንቅልፋችን ነቅተን፡ ገና በየአልጋችን ሳለን፡ ከተማሪዎቹ አንዱ፡ ዓለማየሁ መልአኩ የተባለው፡ "ዛሬ ሌሊት በሕልሜ፡ ያየሁትን ልንገራችሁ!" አለና፡ ኹሉም፡ ያን ሕልሙን ለመስማት፡ አቀብቁበ ሳለ፡ ባለሕልሙ፡ በመገረምና በመደነቅ፡ "'ኤርምያስ እኮ አበደ!' ስል አደርኩ! ምንድር ነው ይኼ ነገር እባካችሁ?" አለ፡፡ ወዲያው፡ ከአድማጮቹ ተማሪዎች መካከል አንዱ፡ አክሊሉ ሥዩም የሚባለው፡ "እኔ ልተርጉምላችሁ!" ብሎ ሕልሙን ተረጉመውና ተሣሥቀን አሳለፍነው፡፡

ያ፡ የሕልሙ ትርጓሜ ግን፡ ዛሬ ለእኔ ትዝ አይለኝም፤ በዚያን ጊዜ፡ እኔም በበኩሌ፡ ያን፡ የሕልሙን ትርጉም፡ ከቁም ነገር አላገባሁትም ነበርና፡ ይህን ያህል አላጤንኩትም ነበር፡፡ ከባለሕልሙ፡ ከአቶ ዓለማየሁ ጋር፡ ከቅርብ ዓመታት በፊት፡ በአካለ ሥጋ ተገናኝተን ሳለ፡ ይህንኑ ሕልሙን፡ ከ፵፯ ዓመታት በኋላ፡ ራሱ አስታውሶ ነገረኝ፡፡

ለምን አስታውሶ ሊነግረኝ እንዳሰበም፡ በዚያች አፍታ አልገባኝም፤ እንዲያው ገርሞኝ፡ ዝም አልኩ። አሁን ሳስበው ግን፡ በአሁኑ ጊዜ፡ እርሱና እርሱን የመሰሉት ጭምር፡ አስተሳሰባቸውና ድርጊታቸው፡ ከጊዜው ጋር ተለዋውጦ፡ እኔው ብቻ፡ ከጥንታዊው፡ የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን አቋም "አልነዋወጥም!" በማለት፡ እንዲህ ስንገታገት ስላየና በዚህ ረገድ፡ የምናገረውን፥ የምጽፈውንም ኹሉ ስለተመለከተ፡ "ምናልባት፡ ይህን ኹኔታዬን፡ እንደ'እብደት' ቆጥሮት ይኾን?" ብዬ እስከመጠራጠር ደረስኩ።

ይህን ጥርጣሬዬን፡ የበለጠ ያጠናከረብኝ ደግሞ፡ ያን፡ የመጨረሻ ግንኙነታችንን ተከትሎ፡ ወዲያው፡ ከሕልሙ ተርጓሚና በኢትዮጵያዊነት የሃይማኖት አቋሙ፡ ጸንቶ ካገኘሁት፡ ከእልፍ አለቃ (Colonel) አክሊሉ ጋር፡ ከረዥም ዘመን መለያየት በኋላ፡ መጀመሪያ፡ በስደት አገር ሣለሁ፡ ባልተጠበቀ አጋጣሚ፡ በደብዳቤ መጻጻፍ፥ ቀጥሎም፡ በዓይነ ሥጋ፡ እንደገና በመተያየት፡ መንፈሳዊ ጓደኝነታችንን ለመቀጠል በቅተን፡ የሕልሙን ነገር ማስታወሳችንና በጥልቅ የትዝታ ስሜት መጫዋወታችን ነው።

ታዲያ፡ ያ ሕልም፡ እንደተቃራኒዎቼ አስተሳሰብ፡ ዛሬ እኔ፡ እያካኼድኩት ባለው "የእብደት" ድርጊት፡ ትርጓሜውን ማግኘቱ ይኾን? ወይስ፡ አሁንም፡ "ጊዜ ይፍታው!" ብለን እንተወው!?

የሕልሙ ቀጥተኛ ትርጓሜ፡ በቁሙ፥ በሥጋ፡ "እብደት" ሊኾን እንደማይችል የሚያመለክቱ፡ ከሕልሙ በኋላ የደረሱና ለእኔ የሚደንቁኝ፡ አንዳንድ፡ የልጅነት ድርጊቶቼ ትዝ ይሉኛል። እነዚህም፡ የሕልሙ ትርኢት የተፈጸመባት፡ የሐረሩዋ ምድርና የቤተሰብ ናፍቆቱን መቻል አቅቶኝ፡ ለገናና ለፋሲካ ወደአዲስ አበባ የመጣሁ ብኾንም፡ በዚያች ምድር ያሳለፍሁት የአንድ ዓመት ቆይታዬ፡ ስለሰው ልጅ ሕይወት ትርጉም፡ ጥልቅ በኾነ መንፈሳዊ ስሜት፡ ካሳደሩብኝ የምርምር ግንዛቤ የተነሣ፡ ያስገኟቸው ፍሬዎች ናቸው። ጥቂቶቹንም ለመጥቀስ ያህል፡ ከሐረር፡ ወደተወለድኩባት አዲስ አበባ፥ ከመምህራን ማሠልጠኛ፡ ወደቆየሁባት ትምህርት ቤቴ፡ ወደዳግማዊ ምኒልክ እንደተመለስኩ፡ ወዲያው፡ በ፲፰ (አሥራ ስምንት) ዓመታት ዕድሜዬ፡ የደረስኳቸው፡ "እየው ያን መከራ! የደስታ ጮራ!" የሚለው፡ በትምህርት ቤቱና በወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር አዳራሾች ተደጋግሞ፡ ለሕዝብ የታየው ተውኔትና "ምናሴ! የመከራዬ ደስታ፡ ዓለምን ረታ!" የሚለው፡ ለኀትመትና ለሕዝባዊ ምንባብ የበቃው መጽሐፌ ናቸው።

ተውኔቱም፥ መጽሐፉም፡ የያዟቸው መልእክታት፡ እንደትንቢት ኾነው መፈጸማቸውን፡ ተውኔቱን ያዩት፥ መጽሐፉንም ያነበቡት፡ ራሳቸው ምስክሮች ናቸው። በተውኔቱ ውስጥ፡ ከዋክብት ኾነው፡ በባልና ሚስትነት የተጫወቱት፥ በመጽሐፉም ዝግጅት፡ ደራሲና ረዳት ኾነው የተባበሩት፡ ኹለት ተማሪዎች፡ የዛሬዎቹ ባልና ሚስት፡ ባለቤቴና እኔ፡ ከምስክሮቹ መካከል እንገኛለን። ስለዚህ ተውኔት፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!" በሚለው መጽሐፌ ውስጥ፡ በ"ትንቢተ ኤርምያስ" ምዕራፍ፡ በመጠኑ የታተተውን፡ አንባቢዎች ተመልክታችሁታል፤ ስለ"ምናሴ" መጽሐፍም፡ በዚህ ድርሰት ውስጥ የተሰጠውን ሐተታ ትመለከቱታላችሁ።

ከትምህርቱ ዓለም ወደሥራው ዓለም ከተሸጋገርሁ በኋላ፡ ያሳለፍሁት ዘመንና ኅብረተሰቡ ምን ዓይነት እንደነበረ ለማስረዳት፡ በአገልግሎት ላይ እያለሁ፡ ከገጠሙኝና ግራ አጋብተውኝ ከነበሩ፡ እንግዳ ነገሮች መካከል፡ አንዱን፡ ከዚህ ጋር አያይዤ እንድጠቅሰው እገደዳለሁ።

ዘመኑ: ከደርግ በፊት: የነበረው ጊዜ ነው፤ እኔም: የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤትና የብሔራዊው የሕዝብ እንደራሴዎች ምክር ቤት አባል ከመኾን ጋር: በመካነ ሰማዕት ቅዱስ ቂርቆስ ደብር አስተዳዳሪነት የማገለግልበት ነበር:: በዚያ አገልግሎቴ: ጽላቱ: ከዚሁ ደብር እየወጣ ይከበር የነበረውን: በቀድሞው: የአየር ማረፊያ አጠገብ የተሠራውን የብሥራተ ገብርኤልን ቤተ ክርስቲያን: ጽላቱንና ካህናቱን: በግል ተሽከርካሪዬ ከማመላለስ ጀምሮ: ዛሬ ሕንፃ ቤተ ክርስቲያኑ ያረፈበትን ቦታ እስከመረከብ በደረሰ ኃላፊነት: ተግባሬን ለመፈጸም: ከፍተኛ ጥረት አደርግ ነበር:: የዚህኑ ቤተ ክርስቲያን ቦታ: ሕጋዊ ቢጋሩን (carta ካርታውን) አስነሥቼ ለመረከብ: የግል ጊዜዬን፥ ገንዘቤንና ጉልበቴን በመሠዋት: በየዕለቱ: ጧት: መሐንዲሶቹን: ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት: ዛሬ: ቤተ ክርስቲያኑ እሚገኝበት ቦታ አድርሼ: ወደምክር ቤት ሥራዬ እኼድና በምሳ ሰዓት እንደገና መጥቼ: ወደመሥሪያ ቤታቸው እመልሳቸዋለሁ:: መሐንዲሶቹ ቅያሳቸውን አከናውነው እስኪጨርሱ ድረስ: ይህ: በየዕለቱ: የምፈጽመው ግዳጅ ነበር:: በዚህ መልክ አካኺደው የነበረው አገልግሎት: ለካ: በሌላ ተቃራኒ ገጽታው ይታይ ኖርዋል:: ለካ: ዘመኑ: "ተሾሞ ያልበላ፥ ሲሻር ይቆጨዋል!" የሚለውን ምሳሌ በመከተል: ማናቸውም ሰው: በተለይም: በሥልጣን ላይ ያለ: የተመደበበትን ተግባር: በታማኝነት ለመፈጸም ሲተጋ ከታየ: እንዲያ የሚሠራው: የአገልግሎት ግዳጁን በትክክል ሊወጣ ሳይኾን: "ለግል ዓላማውና ጥቅሙ ነው" ተብሎ የሚታሰብበት ኖርዋል! በጊዜው የሰፈነው የአሠራር ፈሊጥ: እንዲያ መኾኑን: እኔ ጨርሶ አላውቅም፤ ስለዚህ: እኔ: ያን: የጋራ ጉዳይ: ከግብ ለማድረስ: በየዕለቱ የማደርገው ከፍተኛ ጥረት: በኅብረተሰቡ ዘንድ: በዚሁ ሐሳዊ መልኩ ታይቶ: "የቦታውን ቢጋር የሚያሠራው: በቤተ ክርስቲያኑ ስም ሳይኾን: በራሱ ስም ነው፤" የሚል ሐሜታ: በስፋት ይነዛ ኖሮ: ይህንኑ: በሥራው ይተባበሩኝ ከነበሩት ተመራጮች አንደበት ሳይቀር ሰማሁት::

በዚያን ጊዜ: ጉዳዩ: በኅብረተሰቡና አብረውኝ በነበሩት ተመራጮች ዘንድ: በግልጽ ታውቆ፥ እኔም: "ተግባሬ ነው" ብዬ: በቅንነት የፈጸምሁት: ያ ሥራ: ለግል ዓላማዬና ጥቅሜ አስቤ እንዳደረግሁት ተቆጥሮ: በይፋ እስከመነገር በመድረሱ: በኅብረተሰቡና በእኔ ዘንድ የነበረው የአስተሳሰብ አቋም: የቱን ያህል የተለያየና የተቃረነ እንደነበረ ተረዳሁ:: በመጨረሻ: የቦታው ቢጋር: እንደሐሜቱ ሳይኾን: በቤተ ክርስቲያኑ: ስም መኾኑን የምታረጋግጠው እውነት: ገሃድ ኾና ስትወጣ: ለሐሜተኞቹ የተረፋቸው: ኃፍረት ብቻ ነበረ:: ለእኔ ግን: ነገሩ: ግራ የሚያጋባና እንግዳ ነገር ብቻ ሳይኾን: አስደንጋጭና የአድናቆት ስሜትን ፈጥሮብኝ ያለፈ ድርጊት ኾነ!

## ስለአንባቢው ብቅዓት::

በመደምደሚያው: የእግዚአብሔር እውነት የኾነችውን: ይህችን መልእክት: ለአንባቢዎቼና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ኹሉ በማድረስ: ተልእኮዬን ስፈጽም: የቀረችኝን ቁም ነገር እየገለጽኩ ነው፤ ይህችም ቁም ነገር: በመጀመሪያ: ይህን መጽሐፍ: ከዳር እስከዳር: በንባብ ለመውጣት ቀርቶ: ወደውስጥ ገባልጦ ለመመልከት እንኳ: የፈቃደኛነትና የፍላጎት ኃይል የሚኖራቸው አንባቢዎች: መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው: የእግዚአብሔር ወገኖች ብቻ መኾናቸውን የምታረጋግጠው እውነት ናት::

የዲያብሎስ ርኩስ መንፈስ ያደረበት፡ ሌላው ሰው ግን፡ ይህን መጽሐፍ፡ "አትንኩት!" እያለ፡ ውስጥ ውስጡን፡ በሐሜትና በተንኮል ከማስወራት በቀር፡ እንኳንስ፡ ሊመለከተውና ሊያነብበው፥ በእጁም ሊነካው አይችልም! በአካባቢውም እንኳ ሊደርስ ከቶ አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም፡ መጽሐፉ፡ ገና ሲገለጥ፡ አስቀድሞ ተጽፎ የሚነበበው፡ የሥላሴን፥ የኢየሱስ ክርስቶስንና የድንግል ማርያምን ስሞች የሚያነሣው፥ ኢትዮጵያውያንም፡ በመስቀል አማትበው የሚደግሙት፡ የጸሎት መክፈቻ ቃል፥ ቀጥሎ በሚገኘው ገጽ የሚታየው ደግሞ፡ በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና በኅብረ ቀለማት የደመቀው፥ "ድል አድራጊው የይሁዳ አንበሳ" ወይም "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የተባለው፡ የኢየሱስ ክርስቶስንና "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች" ወይም "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የተባለችው፡ የድንግል ማርያምን ስምና ማንነት የሚገልጸው መለኮታዊው ማኅተም በመኾኑ ነው፡፡

ዲያብሎስና ሠራዊቱ፡ ርኵሳን መናፍስት፡ በእነርሱ አድረው፡ የሚመሩዋቸው፡ ሰዎችም ኾኑ ድርጅቶች፡ ከኹሉ ይልቅ የሚጠሉት ምንድር ነው? ስማቸው እንዳይጠራባቸውና ምልክታቸው እንዳይገኝ የሚጥሩትስ፡ የእነማንን ነው? ስማቸው ሲጠራባቸውና ሲደገንባቸውም፡ መድረሻ እንዲያጡ የሚያደርጓቸው፡ የመንፈስ ቅዱስ መሣሪያዎች የትኞቹ ናቸው? ኢየሱስ ክርስቶስ ተወልዶና ተሰቅሎ፡ እነዚህን የክፋት ኃይላት፥ ኃጢአትንና ሞትን ድል ያደረገባቸው፡ የድንግል ማርያም ስምና የመስቀሉ ምልክት አይደሉምን?

እንግዲህ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በራሷ በድንግል ማርያም፥ በካህኑ በዘካርያስና በሚስቱ በኤልሣቤጥ፥ ከዚያም አልፎ፡ በዚችው በኤልሣቤጥ ማሕፀን ተፀንሶ በነበረው፡ በመጥምቁ ዮሐንስ ላይ አድሮ፥ እንዲሁም፡ ቀደም ብሎ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ገብርኤል፡ ኹሉም፡ በተባበረ አንደበት፡ እንዲያ ያወደሷትንና ያመሰገኗትን፥ ከዚያም ጋር፡ በቃና ዘገሊላ የሠርግ ቤት ተገኝቶ፡ ራሱ ልጇ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ሳይቀር፡ ማንነቱን ለዓለም የሚገልጥበት ጊዜው ሳይደርስ፡ እንዲያደርገው ያዘዘችውን፡ የአማላጅነት ቃሏን የፈጸመላትን፡ እመቤታችንን ድንግል ማርያምን የማይወድድና "ብፅዕት" የማይላት፡ ፀረ ማርያም የኾነ፡ ሰውም ኾነ መንፈስ፡ የዲያብሎስ እንጂ፡ "የእግዚአብሔር ሰው፡ ወይም የእግዚአብሔር መንፈስ ነው" ሊባል፡ ከቶ አይቻልም፡፡ ይህን ምስክርነትና ከላይ፡ "ማንም ሰው፡ በመንፈስ ቅዱስ ካልኾነ በቀር፡ ይህን መጽሐፍ ማንበብ አይቻለውም!" ያልኩት፡ ስለዚህ መኾኑን፡ እውነተኞቹና ታማኞቹ ኢትዮጵያውያን ምእመናንና ምእመናት ኹሉ፡ ደህና አድርገው ሊያውቁት ይገባል፡፡

ይህንንም፡ *"ከእግዚአብሔር የኾነ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል! እናንተ፡ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና፡ ስለዚህ አትሰሙም!"* የሚለው፡ የጌታችን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ቃልና ዮሐንስ ወንጌላዊው፡ *"ወዳጆች ሆይ! መንፈስን ኹሉ አትመኑ! ነገር ግን መናፍስት፡ ከእግዚአብሔር ኾነው እንደኾነ፡ መርምሩ! በኢየሱስ ክርስቶስ የማያምኑ፡ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት፡ ወደዓለም ወጥተዋልና፡፡ እንግዴህ፡ የእግዚአብሔርን መንፈስና የሐሰትን መንፈስ፡ ለይታችሁ የምታውቁበት መንገድ፡ እንዲህ ነው፤ ይኸውም፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰው ሥጋ መምጣቱን፡"* ማለትም፡ ከድንግል ማርያም፡ ፍጹም ሰው ኾኖ መወለዱን፥ በዚህም፡ የእርሷን እናትነትና የእርሱን ልጅነት *"የሚያምን መንፈስ ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር ነው፡፡*

"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በሰው ሥጋ መምጣቱን፡" ማለትም፡ ከድንግል ማርያም፡ ፍጹም ሰው ኾኖ መወለዱን፥ በዚህም፡ የእርሷን እናትነትና የእርሱን ልጅነት "የማያምን መንፈስ ኹሉ፡ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም፡ የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ እርሱም፡ እንዲመጣ ሰምታችኋል፤ አሁንም እንኳ ፈጽሞ መጥቶ፡ በዓለም አለ። ልጆች ሆይ! እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ! አሸንፋችኋቸውማል፤ በዓለም ካለው ይልቅ፡ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና። እነርሱ፡ ከዓለም ናቸው፤ ስለዚህ፡ ከዓለም የኾነውን ይናገራሉ፤ ዓለሙም ይሰማቸዋል። እኛ፡ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልኾነ፡ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስና የሐሰትን መንፈስ፡ በዚህ ለይታችሁ ታውቃላችሁ!"፥ እንዲሁም፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፡ "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን፡ የእግዚአብሔር ኃይል ነው!" ብለው የጻፉቸው ቃላት ያረጋግጣሉ።[፲፮]

## የመቅድሙ ማጠቃለያ።

መጽሐፉን አንብበው ለሚፈጽሙት ኹሉ፡ ራሳቸውን፡ በንስሓ አንጽተውና በሥጋ ወደሙ አጽድቀው፡ ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ቅዱስ አንድ ይኾኑ ዘንድ፡ ያለኝ፡ የመጨረሻ ማሳሰቢያ፡ እንዲህ በሚለው፡ በእግዚአብሔር ቃል ይጠቃለላል፦ "ለእኔም፡ 'ዘመኑ ቀርቧልና፡ የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማንተም አትዝጋው! ዓመፀኛው፡ ወደፊት ያምፅ! ርኵሱም፡ ወደፊት ይርከስ! እውነተኛውም፡ ወደፊት እውነትን ያድርግ! ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ!' አለ። እነሆ በቶሎ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም፡ እንደሥራው መጠን እከፍል ዘንድ፡ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ። አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው፡ እኔ ነኝ።"[፲፯]

ይህ፡ በእኔ የተፈጸመው ተልእኮ፡ በግሌ ሳይኾን፡ በቀደሙት ዘመናት፡ በነቢዩ ኤርምያስ፥ በራሱም በኢየሱስ ክርስቶስ እንደታየው፥ እንዲሁም በሐዋርያው ጳውሎስ አድሮ፡ ለየጊዜያቸው ትውልድ የተናገረው፡ ያው አንዱ እግዚአብሔር፥ ቃሉና መንፈሱ፡ አሁን ላለውም፡ ለዚህ ትውልድ፡ ያንኑ የቸርነት ሥራውን፡ መድገሙ መኾኑን ነው። ይህ መለኮታዊ እውነት፡ የማይታበል መኾኑን፡ የሚከተሉት ጥቅሶች በየመልኩ ያረጋግጣሉ፦ ሀ) እግዚአብሔር፡ በነቢዩ ኤርምያስ አንደበት፦ "ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፤ በልባቸውም እጽፈዋለሁ። ...እያንዳንዱ ሰው፡ ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም፡ ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!' ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!" ብሎ ተናገረ።[፲፰] ለ) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌል፦ "'ኹሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይኾናሉ' ተብሎ በነቢያት ተጽፏል፤ እንግዴህ፡ ከእግዚአብሔር አብ የሰማ፥ የተማረም፡ ኹሉ፡ ወደእኔ ይመጣል!" ሲል አወጀ።[፲፱] ሐ) ሐዋርያው ጳውሎስ፦ "በእኔ የተሰበከ ወንጌል፡ እንደሰው እንዳይደለ አስታውቃችኋለሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ፤ እኔ፡ ከሰው አልተቀበልሁትም፥ አልተማርሁትምም!" በማለት ጽፏል።[፳]

\+ \+ \+

# ክ ፍ ል

# አ ን ድ

ኢትዮጵያ፡



ኪዳነ አዳም ወሔዋን::
(ሓተታው፡ በገጽ ፺፩-፺፫ ይገኛል::)

# የእግዚአብሔር እውነት

## ስለኢትዮጵያ ማንነትና ምንነት

## የምትሰጠው ምስክርነት

ኢትዮጵያ፡



ኪዳነ ኖኅ።
(ሐተታው፡ በገጽ ፳፱-፳፫ ይገኛል።)

# ምዕራፍ ፭

## ኢትዮጵያ፥ ኢትዮጵያዊው እና ኢትዮጵያዊነት።

ረዥም ዕድሜ ባለውና ሕያው በኾነው: በኢትዮጵያ ትውፊት: ህልውናን አግኝተው፥ እውን ኾነውና በሰውነት ጎልተው የሚታዩ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ: በክብር ተመዝግበው የሚነበቡ፥ እግዚአብሔር አምላክ: ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ: ከሰው ልጆች ጋር የተካየዳቸው: ሰባት ኪዳናት ይገኛሉ።

እነዚህም ኪዳናት: ከዚህ እንደሚከተለው የተዘረዘሩት ናቸው:-

የመጀመሪያው: በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ ምልክትነት የሚታወቀው: "ኪዳነ አዳም"[፳፩]፥

ኹለተኛው: በቀስተ ደመና ምልክትነት የሚታወቀው: "ኪዳነ ኖኅ"[፳፪]፥

ሦስተኛው: በኅብስትና ጽዋ ቁርባን ምልክትነት የሚታወቀው: "ኪዳነ መልከ ጼዴቅ"[፳፫]፥

አራተኛው: በግርዛት ምልክትነት የሚታወቀው: "ኪዳነ አብርሃም"[፳፬]፥

አምስተኛው: በጽላትና ታቦት ምልክትነት የሚታወቀው: "ኪዳነ ሙሴ"[፳፭]፥

ስድስተኛው: በዘውድ ምልክትነት የሚታወቀው: "ኪዳነ ዳዊት"[፳፮]፥ የተባሉት ሲኾኑ: ከላይ የተጠቀሱት: የቀደሙት ስድስቱ ኪዳናት ታድሰው የተዋሃዱበትና ለዘለዓለም ጸንተው የሚኖሩበት:

ሰባተኛውና የመጨረሻው ደግሞ: ኢየሱስ ክርስቶስ: ከድንግል ማርያም ተወልዶ: በተሰቀለበት ሥጋውና ባፈሰሰው ደሙ ምልክትነት: የተገለጸውና የሚታወቀው: "ኪዳነ ምሕረት" የተባለው አዲስ ኪዳን ነው።[፳፯]

እነዚህ ኪዳናት: የየቅል መታወቂያቸው: ከላይ እንደሠፈረው: እውን በኾኑ: የተለያዩ ምልክቶች የተገለጸ ሲኾን: በሰውነት ገዝፈው የታዩት ደግሞ: ለፈጣሪያቸው ባላቸው እውነተኛ ፍቅር: እርሱን አምላካቸውን ባስደሰቱ ትሑታን ግለሰቦች ሕያው አካል ላይ ነው።

እኒህ ግለሰቦች: በአካላዊውና በመንፈሳዊው አግጣጫ: በተለያዩ መልኮች የመጡባቸውን ታላላቅ ፈተናዎች: ብቻቸውን ተቋቁመው በማሸነፍ: በተጐናጸፉት የድል አክሊል: ከሰው ልጆች መካከል ብርቅ ኾነው ሊታዩና ከፈጣሪያቸው ከእግዚአብሔር ጋር: የየራሳቸውን ኪዳን: በነፍስ ወከፍ ሊካየዱ የቻሉ ገድለኞች ለመኾን በቅተዋል። እያንዳንዳቸውም: የሰውን ዘር በመወከል: የመለኮታዊው ልዩ ቃል ኪዳን ተዋዋይ ኾነው ለመመረጥ: በፊቱ ሞገስን በእውን ከማግኘታቸው አስቀድሞ: ለእርሱ ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር: እውነተኛ መኾኑ ሊረጋገጥ ስለሚገባ: እኒያ ፈተናዎች: እሳት ኾነው ሊያጠሩዋቸው: በየግላቸው ላይ ነድደውባቸዋል።

ከላይ የተዘረዘሩት፡ ሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት፡ የኢትዮጵያን እና የኢትዮጵያዊዉን/ዊቷን ህልውና፥ ሕይወትና ማንነት ያስገኙ፡ ሰባቱ ባሕርያት ናቸው:: በሌላ አገላለጽ፡ ኢትዮጵያ ወይም ኢትዮጵያዊው/ዊቷ ማለት፡ እኒህ ሰባቱ ኪዳናት ናቸው! አዎን፥ እኒህ ሰባቱ ኪዳናት፡ ኢትዮጵያ ወይም ኢትዮጵያዊው/ዊቷ ማለት ናቸው:: ያለእነዚህ ሰባቱ ኪዳናት፡ ወይም ከእነርሱ ውጪ በሚያደርግ፡ ሌላ የህልውና ሥርዓት ወይም ርእዮተ ዓለም፡ ኢትዮጵያ የምትባል አገር የለችም፤ ልትኖርም አትችልም:: ወይም ኢትዮጵያዊ የሚባል ሰብአዊ ፍጡር ወይም ሕዝብ የለም፤ ሊኖርም ከቶ አይችልም::

በዚህ መሠረትና ከዚህ የተነሣ፡ ይህች ኢትዮጵያ፡ እውነተኛዪቱ ኢትዮጵያ ብቻ ሳትኾን፡ እውነተኛዪቱ እስራኤል ጭምር፥ እኒህ ኢትዮጵያውያንም፡ እውነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾኑ፡ እውነተኞቹ እስራኤላውያን ጭምር እንደኾኑ፡ የብሉዩንና የሐዲሱን ኪዳናት አጠቃልለው የያዙት ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በዚያች በእግዚአብሔር የእውነት ቃል፡ ልዩ እውቅና ሰጥተው፡ በማያወላውልና በማያዳግም ኹኔታ አጽድቀውታል:: ይህ እውነታ፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ባሉት ዓምዶች ላይ በሠፈሩት ሰፊ ሐተታዎች ተብራርቷል::

የኢትዮጵያ ህልውናና የኢትዮጵያዊ ወይም የኢትዮጵያዊት ሕይወት፡ ኹለቱም፡ በእነዚህ በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ላይ በጽኑ ተመሥርተው፡ በተዋሀዶ የተሣሠሩ ናቸው:: ይህንንም፡ ከእነዚሁ ኪዳናት መንጭተውና በእነዚሁ ኪዳናት ለምልመው የሚታዩት፡ የኢትዮጵያውያን፡ የሃይማኖት፥ የባህልና የማኅበራዊ ኑሮ ሕይወታቸው ድርና ማግ ብቻ ሳይኾን፡ በትምህርት አሰጣጥ፥ በሀብት ልማትና በሥነ መንግሥት አመራር ረገድ፡ በሥርዓት የሚከተሏቸው፡ ሕያዋን የኾኑት አምላካውያት ሕጎቻቸው ጭምር፡ በገሃድ አረጋግጠው ያሳያሉ:: እንግዴህ፡ ይህ ነው፡ ኢትዮጵያዊነት::

## "ኢትዮጵያ" የሚለው ስያሜ ከየት ተገኘ?

"ኢትዮጵያዊነት" ከሚለው ቃል ጋር፡ የጥሬ ዘርና የምሥጢር፥ የዘይቤና የትርጉም ተዘምዶ ያላቸው፡ በዓለም ሕዝቦችና ቋንቋዎች ዘንድ የታወቁ፡ አንዳንድ ይፋ ቃላት አሉ:: ከእነዚህ መካከል፡ የሚከተሉት ተጠቅሰዋል:-

-"ኢትዮጵያ" ለማለት፡ *"ጦቢያ"* የሚለው ትውፊታዊ፥ መጽሐፋዊና ሕዝባዊ ቃል፤

- ጥንታውያን የዓለም ፈላስፎችና ደራስያን፡ የኢትዮጵያን፡ ምድራዊት ገነትነትና የኢትዮጵያውያንን መልአካዊ አኗኗር፡ በመንፈስ በማየትና በዜና በመስማት፡ የኢትዮጵያን፡ ማንነትና የኢትዮጵያዊነትን ምንነት፡ በየጽሑፋቸው ለመግለጽ ይጠቀሙበት የነበረው፥ ይህን የመሰለውንም ሕይወት፡ በምድር ላይ ለመፍጠርና ለማግኘት ይቻላል በሚል እምነት፡ የሰው ልጅ፡ ዛሬም እየተጠቀመበት የቀጠለው፡ *"ዩቶፒያ" (Utopia)* የሚለው የቅርስ ቃል፤

- ጥንት: በዛሬዪቱ ኢትዮጵያ: ምድራዊ ክልል ውስጥ ይኖር የነበረ: ዓሣ በላተኛ ሕዝብ: ተለይቶ ይጠራበት የነበረው: *"ኢትዮፖጊ" (Ichthyophagi)* የሚለው የስያሜ ቃል፤

- ዕብራውያን: በዕብራይስጥ ቋንቋቸው: "ኢትዮጵያ" ወይም "ኢትዮጵያዊ" ለማለት: የሚጠቀሙበት: *"ኵሽ"* የሚለው የተጸውዖ ቃል፤

- ዓረቦች: "ኢትዮጵያ" ወይም "ኢትዮጵያዊ" ለማለት የሚጠቀሙበት: *"ኻበሽ"* ወይም *"አበሻ"* የሚለው የዓረብኛ መጠሪያ ቃል፤

- እንግሊዞች: ይህን የዓረብኛውን ቃል ቈልምመው: ወይም "አቢስ" የተባለው የነገድ አባት ዝርያዎች ናቸው ለማለት የተጠቀሙበት: *"አቢሲንያ"* የሚለው መለያ ቃል፤

- በመጨረሻም: ኢትዮጵያውያን: በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው መሠረትነት በሠመረው የኅብረተሰብአዊነት ህልውናቸው የሚታወቁበትና የሚጠሩበት: *"ዐምሐራ"* የሚለው የውህደት ስም::

"ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል: "ኢትዮጲስ" ከሚለው: ከመጀመሪያው መልከ ጼዴቅ: በውህደት ለበቀለው: የዘር ግንድ ከተሰጠው ስም የተገኘ አጠራር ሲኾን: ከላይ እንደተጠቀሰው: ጥንታውያኑ የዓለም ሕዝቦች: ይልቁንም ግሪኮች: ከሌሎቹ ነገዶች የመልክ ቀለማት: የተለየና የታወቀ የኾነውን: የኢትዮጵያውያንን የመልክ ዓይነት: ራሱን አስችለው: ለመጠቆም ሲሉ: በዚሁ: "ኢትዮፕስ" (Aethiops) በሚለው ቃል የተጠቀሙ መኾናቸውን: ሕያው የኾነው: የኢትዮጵያውያን ትውፊት: በአጽንዖት ያመለክታል:: በዚህ የገላ ቀለም: ተለይቶ የታወቀውን: ይህን ኢትዮጵያዊ መልክ: በባለቤቱ የነገድ ማንነትና ምንነት ረገድ: ብቸኛ የኾነ: የማይለወጥ ባሕርይና ገጽታ ያለው መኾኑን: አምላካዊው የትንቢት ቃል: እንዲህ ሲል: በሥዕላዊ አቀራረብ አሳምሮ በማስረዳት: በነቢዩ በኤርምያስ አንደበት: ገልጾታል:- *"በውኑ፥ ኢትዮጵያዊ: መልኩን፥ ወይስ ነብር: ዝንጕርጕርነቱን ሊለውጥ ይችላልን?"*[፳፰]

## ኢትዮጵያ:
## ስለዐምሐራነት ስትፋረድ!

ከላይ ከተጠቀሱት: ከ"ኢትዮጵያ" ጋር የተዛምዶ ግንኙነት አላቸው ከተባሉት ቃላት መካከል: በመጨረሻ የተወሳው: "ዐምሐራ" የሚለው መጠሪያ ቃል: ለተነሣንበት አርእስት: የበለጠ አግባብነት አለው::

የዚህም ምክንያት: ኢትዮጵያ የቆመችለትን እምነት የሚጻረሩ: አንዳንድ ባዕዳንና የአገር ተወላጆች: በዛሬው ዘመን፥ በቅርቡም: እስካለፈው ምዕት ዓመት ድረስ: በሕዝቡና በአገሪቱ ላይ ሊጭኑ ያቀዱትን: የየራሳቸውን የገዢነት ቀምበርና የግል ጥቅም ፍላጎታቸውን ዓላማ: እውን ለማድረግ ሲሉ: ስለዚሁ: "ዐምሐራ" ስለሚለው አገር-አቀፍ ስያሜ: ኾን ብለው የፈጠሩት: እጅግ የረቀቀ፥ የስሕተትና የቅራኔ ትርጓሜ ስላለ ነው:: ስለዚህ: እዚህ ላይ የተለየ ትኵረት ተሰጥቶት: የቃሉን ምንጭና እውነተኛ ትርጉም በሚመለከት: በቂ ማስረጃዎችን ከማቅረብ ጋር: አጠር ባለ ሐተታ: ስለቃሉ ዓቢይ ቁም ነገር: መተንተንና ማብራራት: ግዴታ ይኾናል::

"ዐምሐራ" የሚለው ቃል፡ መልእክትና ትርጒም ባለው ምክንያት፡ በኢትዮጵያ ምድር ለሚኖረው፡ ለአብዛኛው የአገሪቱ ነባር ሕዝብ የተሰጠ ትውፊታዊ ስያሜ ነው:: ቃሉ፡ ከግእዝ ተገኝቷል:: በግእዝ፡ "ዐም" ማለት፡ "ሕዝብ"÷ "ሐራ" ማለት ደግሞ፡ "ነጻ" ማለት ነው:: ስለዚህ "ዐምሐራ" የሚለው ስያሜ፡ የቃል ለቃል ትርጒሙ፡ "ነጻ ሕዝብ" ማለት ሲኾን፡ ይህም ትርጒም፡ የእውነተኛ ኢትዮጵያዊን ማንነት ከሚገልጹት ዓበይት ባሕርያት መካከል፡ አንዱ መኾኑን በግልጽ ያመለክታል::[፹፱]

ግእዝ፡ ራሱን የቻለ፡ ፊደል ያለው፡ የኢትዮጵያውያን፡ የመጀመሪያው እናት ቋንቋቸው መኾኑ፡ በዓለም ሕዝቦች ዘንድ ሳይቀር፡ በይፋ የታወቀ ነው::[፺]

የዐምሐራው ኅብረተሰብ፡ መነጋገሪያው ያደረገው ቋንቋ፡ "ዐምሐርኛ" ተብሏል:: የዚህ ኅብረተሰብ፡ የቃል ብቻ ሳይኾን፡ የጽሕፈት መገናኛው ጭምር የኾነው፡ ይህ ልሳን፡ ግንዱ፡ ግእዝ ቢኾንም፡ በጋብቻና በልደት እንደተዋሃደው፡ እንደቋንቋው ባለቤት ኹሉ፡ ዐምሐርኛም፡ ብሔር-አቀፍ ኾኖ፡ በአገሪቱ ውስጥ በሚነገሩት፡ አያሌና የተለያዩ በኾኑ ልሳናት፡ ራሱን ሲያበለጽግ የኖረ ቋንቋ መኾኑ፡ የቃላቱ ቤተ መዛግብት ያረጋግጣል::

"ዐምሐራ" የሚለው ስም፡ ለምሳሌ፡ አገው÷ አርጎባ÷ አፋር÷ ኦሮሞ÷ ጉራጌ÷ ጋፋት÷ ሐዲያ÷ ወላይታ÷ ከምባታ÷ ኵናማ÷ ወይም ትግሬ እንደሚባሉት፡ በየኀጣቸውና በየክልላቸው÷ በየእምነታቸውና በየቋንቋቸው፡ ተለያይተውና ተወስነው፡ በየስማቸው እንደሚታወቁት ብሔሮች÷ ወይም፡ ሴማውያን÷ ካማውያንና ያፌታውያን ተብለው፡ በመላዋ ምድር ላይ ተሠራጭተው እንደሚኖሩት፡ እንደሦስቱ የሰው ዘር፡ የትውልድ ቅርንጫፎች፡ ይህም ኅብረተሰብ፡ "አንድ ነጠላ ጐሣ ወይም ነገድ ነው" ተብሎ፡ ለእርሱ፡ መለያና መታወቂያ ይኾን ዘንድ የተሰጠ ስያሜ አይደለም::

በሌላ አገላለጽ፡ ዐምሐራ፡ የአንድ ጐሣ ወይም የአንድ ነገድ ወይም የአንድ ዘር ወገን አይደለም ማለት ነው:: የቃሉ ፍቺ እንደሚያመለክተው፡ ዐምሐራ፡ በኢትዮጵያ ምድር የሠፈሩ÷ ከተለያዩ ጐሣዎች÷ ነገዶች÷ ዘሮች÷ ቋንቋዎች÷ ባህሎች እና/ወይም ሃይማኖቶች የተውጣጡ ወንዶችና ሴቶች፡ እርስ በርሳቸው በመጋባት፡ በሥጋ፡ አንድ የኾኑበት ህልውና ነው፤ በመንፈስም፡ ቀድሞ፡ በኪዳነ ልቦና÷ ቀጥሎ፡ በኪዳነ ኦሪት÷ በመጨረሻ፡ በኪዳነ ምሕረት፡ የክርስትና ተዋህዶ ሃይማኖት፡ ከእግዚአብሔር በመወለድ፡ ሥጋቸውና ነፍሳቸው÷ እነርሱም፡ ኹላቸው፡ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ፡ ፍጹም አንድ የኾኑበት ሕይወት ነው፤ በአጠቃላይ፡ "ኢትዮጵያዊነት" የተባለውን፡ ዘለዓለማዊ የህልውና ዓላማ፡ በሕያውነት ከግብ ለማድረስ፡ መለኮታዊዉን ጥሪ፡ በፈቃዳቸው ተቀብለው፡ ለእርሱ፡ በጋራ፡ ቃል ኪዳን የገቡና ለሰውም ኾነ ለዲያብሎስ ተገዢ ከመኾን ነጻ ወጥተው፡ በእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት፡ በእኩልነት ፍትሕ በመመራት እየተዳደሩ፡ እንደአንድ ቤተሰብ የሚኖሩበት ሥርዓተ ሀገር ነው::

ዐምሐራው፡ ከላይ እንደተገለጸው፡ የእኒያ፡ እያንዳንዳቸው፡ የየግላቸውን ብሔረኝነትና ጐሠኛነት÷ አምልኮና ልሳን በፈቃዳቸው ትተው፡ ኢትዮጵያዊነትን፡ ከፍጹም ኹለንተናው ጋር፡ በፈቃዳቸውና በሃይማኖት የተቀበሉ፡ የኢትዮጵያ ጥንታውያን ባላገሮች ኅብረተሰብ ስለኾነ፡ ቀጥሎ ባለው ሐተታ እንደሚብራራው፡ ይህ ኅብረተሰብ፡ እውነተኛው ኢትዮጵያዊ ኾኖ ለመገኘት በቅቷል::

እንግዲህ፡ ማንኛውም ግለሰብ፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነት እምኖ፡ የዚህ ኅብረተሰብ አባል ለመኾን፡ በፍጹም ነጻነት ፈቃደኛ ሲኾን፡ የሚፈጸምለት ሥርዓት አለ፤ ይኸውም፡ ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ለአዲሱ ኪዳን ማኅበራዊ ሕይወት የሚያበቃውን ጸጋ የሚጎናጸፍበት ልዩ ሥርዓት ነው፤ እርሱም፡ በሃይማኖት እውቀት፥ በእውነተኛ ንስሓ፥ በክርስትና ጥምቀትና በቅዱስ ቍርባን ምሥጢራት ይፈጸማል:: ለዚያ ግለሰብ፡ ይህ ሥርዓት እንደተፈጸምለት፡ ወዲያው፡ ያ ግለሰብ፡ "ዐምሐራ ኾነ!" ይባላል፤ "ክርስቲያን ኾነ!" ወይም "ኢትዮጵያዊ ኾነ!" ማለት ነው:: "ዐምሐራነት"፡ ኋላ፡ በሥጋ ጋብቻ ጭምር እስኪዋሃዱበት ድረስ፡ በቅድሚያ፡ እንዲህ በመንፈስ የሚወለዱበት ስለኾነ፡ ጐሣ ወይም ብሔር አለመኾኑ፡ በዚህ ይታወቃል::

በዚህ ጊዜ፡ ያ ግለሰብ፡ ኢትዮጵያዊነት፡ በሚያስተማምን ቃል ኪዳን፡ ለዘለዓለም የሚያጐናጽፈውን፡ ያን፡ በመለኮታዊ ጸጋ የተገኘውን ሰብአዊ ነጻነት እንዳይቀዳጅ፡ ከልክሎት ከኖረው፡ ከጠባብ ብሔረኝነትና ከጐሠኝነት፥ ከቋንቋና ከአምልኮ ባዕድ ቁራኝነት፥ ከአጓጉል አስተሳሰብም ቀምበር ተላቅቆ፡ የእውቀት ብርሃን የወጣለትና የነጻነትን አክሊል የተቀዳጀው ኅብረተሰብ አባል ለመኾን የበቃ ይኾናል::

ይህ "ዐምሐራ" የመኾን ምሥጢር፡ "ኢትዮጵያዊ" ከመኾን ጋር የሚመሳሰልና እንደ"ኢትዮጵያዊነት" ኹሉ፡ ያልተቋረጠ ትንግርታዊ ሂደት ያለው ኾኖ ኖርዋል:: "ዐምሐራ ኾነ" ማለት፡ ከላይ እንደተወሳው፡ "ኢትዮጵያዊ ኾነ" እንደማለት ብቻ ሳይኾን፡ በአሁኑ ጊዜ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ፡ በይበልጥ እውቅና እንዳገኘውና በመጨረሻው ዘመን፡ የሰውን ዘር እንደገና አዋህዶ፡ ፍጹም አንድ እንደሚያደርገው፡ እንደአዲስ ኪዳኑ ስያሜ፡ "ክርስቲያን ኾነ" ማለትም ነው:: በዚህ መሠረት፡ ዐይነተኛው (ማለት አማናዊው ወይም እውነተኛው) ዐምሐራ፡ ዐይነተኛው ኢትዮጵያዊ ወይም ዐይነተኛው ክርስቲያን ነው፤ ዐይነተኛው ኢትዮጵያዊ ወይም ዐይነተኛው ክርስቲያንም፡ ዐይነተኛው ዐምሐራ ነው:: እንዲህ ከኾነ፡ እነዚህ ሦስት ስያሜዎች፡ ማለትም፡ ዐምሐራነት፥ ኢትዮጵያዊነት እና ክርስቲያንነት፡ በምሥጢርና በትርጓሜ ይዘታቸው፡ አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል፡ የተመሳሳይነትና የተወራራሽነት ባሕርይ ያላቸው ቃላት መኾናቸው፡ በግልጽ ይረጋገጣል::

ለዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ የዘር ግንድ የኾነው፡ የጥንቱ የዐምሐራ ኅብረተሰብ፡ የኢትዮጵያ ነባር ባላገሮች ከኾኑት፡ ኅዳጣን (ቁጥራቸው አናሳ የኾነ) እና ብዙኃን (ቁጥራቸው በርካታ የኾነ) ብሔረሰቦች ተውጣጥቶና ተዋህዶ የተገኘ መኾኑ፡ ከላይ ተመልክቷል::

የዚያ ጥንታዊ ኅብረተሰብ አባሎች የኾኑት፡ እንያ አባቶችና እናቶች፡ ለቅዱሱ ኪዳን አምላክ፡ ለልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ፡ ራሳቸውን፡ በሃይማኖት በማስገዛት፡ ዘለዓለማዊዉን በረከትና ጸጋ፡ ለልጅ ልጆቻቸው እንደሚያቀዳጅ የተማመኑበትን፡ የኢትዮጵያዊነትን መሠረት፡ በበለጠ አጽንተው ለመቀጠል፡ በስምምነት የሰጡት ውሳኔና ውሳኔውን በሥራ ላይ በማዋል፡ የፈጸሙት ገድል፡ ለዚህ ግዳጃቸው ከከፈሉት መሥዋዕትነት ጋር፡ እጅግ ብልሆች፥ አርቆ አስተዋዮችና ቆራጦች ለመኾናቸው በቂ ማስረጃ ኾኗቸዋል::

እንግዲህ: ማነኛውም ግለሰብ: ወንድ ኾነ ሴት: በዚህ ኢትዮጵያዊነት እምኖ: የዚህ ኅብረተሰብ አባል ለመኾን: በፍጹም ነጻነት ፈቃደኛ ሲኾን: የሚፈጸምለት ሥርዓት አለ፤ ይኸውም: ከመንፈስ ቅዱስ በመወለድ: በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ: ለአዲሱ ኪዳን ማኅበራዊ ሕይወት የሚያበቃውን ጸጋ የሚጎናጸፍበት ልዩ ሥርዓት ነው፤ እርሱም: በሃይማኖት እውቀት፥ በእውነተኛ ንስሓ፥ በክርስትና ጥምቀትና በቅዱስ ቁርባን ምሥጢራት ይፈጸማል:: ለዚያ ግለሰብ: ይህ ሥርዓት እንደተፈጸምለት: ወዲያው: ያ ግለሰብ: "ዐምሐራ ኾነ!" ይባላል፤ "ክርስቲያን ኾነ!" ወይም "ኢትዮጵያዊ ኾነ!" ማለት ነው:: "ዐምሐራነት": ኋላ: በሥጋ ጋብቻ ጭምር እስኪዋሃዱበት ድረስ: በቅድሚያ: እንዲህ በመንፈስ የሚወለዱበት ስለኾነ: ጐሣ ወይም ብሔር አለመኾኑ: በዚህ ይታወቃል::

በዚህ ጊዜ: ያ ግለሰብ: ኢትዮጵያዊነት: በሚያስተማምን ቃል ኪዳን: ለዘለዓለም የሚያጐናጽፈውን: ያን: በመለኮታዊ ጸጋ የተገኘውን ሰብአዊ ነጻነት እንዳይቀዳጅ: ከልክሎት ከኖረው: ከጠባብ ብሔረኝነትና ከጐሠኝነት፥ ከቋንቋና ከአምልኮ ባዕድ ቁራኝነት፥ ከአጓጉል አስተሳሰብም ቀምበር ተላቅቆ: የእውቀት ብርሃን የወጣለትና የነጻነትን አክሊል የተቀዳጀው ኅብረተሰብ አባል ለመኾን የበቃ ይኾናል::

ይህ "ዐምሐራ" የመኾን ምሥጢር: "ኢትዮጵያዊ" ከመኾን ጋር የሚመሳሰልና እንደ"ኢትዮጵያዊነት" ኹሉ: ያልተቋረጠ ትንግርታዊ ሂደት ያለው ኾኖ ኖርዋል:: "ዐምሐራ ኾነ" ማለት: ከላይ እንደተወሳው: "ኢትዮጵያዊ ኾነ" እንደማለት ብቻ ሳይኾን: በአሁኑ ጊዜ: በፍጥረተ ዓለሙ ዘንድ: በይበልጥ እውቅና እንዳገኘውና በመጨረሻው ዘመን: የሰውን ዘር እንደገና አዋህዶ: ፍጹም አንድ እንደሚያደርገው: እንደአዲስ ኪዳኑ ስያሜ: "ክርስቲያን ኾነ" ማለትም ነው:: በዚህ መሠረት: ዐይነተኛው (ማለት አማናዊው ወይም እውነተኛው) ዐምሐራ: ዐይነተኛው ኢትዮጵያዊ ወይም ዐይነተኛው ክርስቲያን ነው፤ ዐይነተኛው ኢትዮጵያዊ ወይም ዐይነተኛው ክርስቲያንም: ዐይነተኛው ዐምሐራ ነው:: እንዲህ ከኾነ: እነዚህ ሦስት ስያሜዎች: ማለትም: ዐምሐራነት፥ ኢትዮጵያዊነት እና ክርስቲያንነት: በምሥጢርና በትርጓሜ ይዘታቸው: አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል: የተመሳሳይነትና የተወራራሽነት ባሕርይ ያላቸው ቃላት መኾናቸው: በግልጽ ይረጋገጣል::

ለዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ: የዘር ግንድ የኾነው: የጥንቱ የዐምሐራ ኅብረተሰብ: የኢትዮጵያ ነባር ባላገሮች ከኾኑት: ኅዳጣን (ቁጥራቸው አናሳ የኾነ) እና ብዙኃን (ቁጥራቸው በርካታ የኾነ) ብሔረሰቦች ተውጣጥቶና ተዋህዶ የተገኘ መኾኑ: ከላይ ተመልክቷል::

የዚያ ጥንታዊ ኅብረተሰብ አባሎች የኾኑት: እንያ አባቶችና እናቶች: ለቅዱሱ ኪዳን አምላክ: ለልዑል እግዚአብሔር ፈቃድ: ራሳቸውን: በሃይማኖት በማስገዛት: ዘለዓለማዊዉን በረከትና ጸጋ: ለልጅ ልጆቻቸው እንደሚያቀዳጅ የተማመኑበትን: የኢትዮጵያዊነትን መሠረት: በበለጠ አጽንተው ለመቀጠል: በስምምነት የሰጡት ውሳኔና ውሳኔውን በሥራ ላይ በማዋል: የፈጸሙት ገድል: ለዚህ ግዳጃቸው ከከፈሉት መሥዋዕትነት ጋር: እጅግ ብልሆች፥ አርቆ አስተዋዮችና ቆራጦች ለመኾናቸው በቂ ማስረጃ ኾኗቸዋል::

# ኢትዮጵያ፡

አዎን! የዐምሐራው ኅብረተሰብ፡ ከአዳምና ሔዋን ተነሥቶ፥ በወንድሙ በቃየል የተገደለው፡ የልጃቸው የአቤል ምትክ በኾነው፡ በእሴት፥ ከዚያ፡ በኖኅና በልጆቹ፡ በሴም፥ በካምና በያፌት ነገዶች ውህደት በተገኘው በመልከ ጼዴቅ አማካይነት ሲወርድ ሲዋረድ የቀጠለው፡ የቅዱሱ ኪዳን ዘር እንደመኾኑ፡ የዚህ ኅብረተሰብ ጥንታውያን አባቶችና እናቶች፡ በሥጋ ለወለዷቸው፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር፡ በውርስ እንዲረከቡ በማድረግ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም፡ ከፍጹምነት ለደረሰው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነት አብቅተዋቸዋል።

እስቲ ዛሬ፡ የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው፡ ወይም፡ ከላይ በጥቂቱ በተወሱትና ከየራሳቸው ጠባብ ብሔረኝነት ጋር ተቆራኝተው በሚገኙት ጐሣዎች ውስጥ አባል ከኾነው ግለሰብ መካከል እንኳ ሳይቀር፡ የትኛው ነው፡ እንኳንስ፡ ከአንድ ነጠላ ጐሣ ይቅርና፡ "ከኹለት ወይም ከሦስት ጐሣዎች ብቻ የተወለድኩ ነኝ" በማለት፡ በሙሉ አፉ ደፍሮ ሊናገር የሚችል? ማንም ሊኖር ከቶ አይችልም። ምክንያቱም፡ ያ ኢትዮጵያዊ ወይም የጐሣ አባል፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ በወላጆቹ የትውልድ ግንድ በኩል፡ በጥቂቱ ወደኋላ ኼድ ብሎ፡ የአያቶቹን፥ የቅድማያቶቹንና የምዝላቶቹን የዘር ሐረግ ቢስብ፡ ራሱን፡ የኅብረብሔር ፍሬ፡ ማለት፡ እያሌ ጐሣዎች የተዋሃዱበት ቅይጥ ፍጡር ኾኖ ያገኘዋል። "ዐምሐራ" ወይም "ኢትዮጵያዊ"፡ ከሚያሰኙት ዓበይት ባሕርያት መካከል ደግሞ፡ ይህ፡ የኅብረ ብሔር ፍሬነት፡ አንዱ፡ ዓይነተኛው ባሕርይ መኾኑን፡ በትኩረት መመልከት ነው።

የዚህ እውነታ አማናዊነትና እርግጠኛነት፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ምድር፥ እንዲሁም፡ በአገር ውስጥ በሚኖሩትና በውጭ አህጉር ተበትነው በሚገኙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሰፍኖ በሚታየው ኹኔታ፡ ጎልቶና ገዝፎ ይታያል። ይኸውም፡ ዓይነተኛው (እውነተኛው) የዐምሐራው ኅብረተሰብ፡ ኢትዮጵያ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ሥር ተዋህዳ የኖረች፡ የማትከፋፈል፡ አንዲት አካል መኾኗን በማመን፡ በጐሣ ወይም በዘር መለያየትን የሚቃወም በመኾኑ ነው።

እንዲያውም፡ ኢትዮጵያዊነት፡ ከዚህ የበለጠ፡ የመጠቀና የጠለቀ፥ የሰፋም ባሕርይ አለው፤ ይኸውም፡ ለኢትዮጵያ፥ እንዲሁም፡ ላለፉትና ለዛሬዎቹ፥ ለወደፊቶቹም ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ ተለይቶና ተወስኖ የተሰጠ፥ እየተሰጠ ያለና የሚሰጥም አለመኾኑ ነው፤ ነገር ግን፡ በዘመነ ሐዲስ ኪዳን፡ ሞክሼው (መሰሉ) እንደኾነው፡ እንደክርስቲያንነት ኹሉ፡ የሰው ዘር በሙላ ተጠቃልሎና በመለኮታዊው መንግሥት ሥር ተዋህዶ፡ አንድ እንዲኾንበት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ለፍጥረተዓለሙ ደህንነትና መልካም ሕይወት፡ አዘጋጅቶ የዘረጋው ዘላለማዊ ዕቅድ ነው እንጂ። ይህም፡ በምድር ላይ ላለው፡ ለሰው ልጆች ችግር ኹሉ፡ የመጨረሻው መፍትሔ እንደሚኾን ይታመናል።

ከዚህ የተነሣ፡ ባንድ ወገን፡ "መላው ዐማራ" በሚል ስያሜ የተቋቋመው ድርጅት፡ በውስጡ፡ "ዐማራ" ከሚያሰኘው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖት ውጪ የኾኑትን ግለሰቦች ጭምር፡ በአባልነት አጠቃልሎ እንዲይዝ በማድረግ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በአገር-አቀፍ ደረጃ፡ "የዐማራው ክልል" በሚል ዕቅድ፡ የተጀመረውን የመከፋፈል ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመሞከር፡ የሚፈጸመው ድርጊት፡ በየመልኩ ሊወገዝ ይገባዋል።

ምክንያቱም: ይህ: በኹለቱም ወገኖች የሚፈጸመው ድርጊት: ዐምሐራን: ከመሠረታዊው: የኢትዮጵያዊነት ባሕርዩ አውጥተው: እንደጎሣ ለማስቈጠር: የኢትዮጵያ የደም ጠላቶች በሚያውጠነጥኑት ሴራና በሚያካኼዱት ዘመቻ ውስጥ ተባባሪ÷ ደጋፊና መሣሪያ መኾኑን: በግልጽ አረጋግጠ የሚያሳይ: የክህደትና የዓመፅ ተግባር በመኾኑ ነው:: ስለዚህ: "ዐምሐራ": ኢትዮጵያዊነትን ሕያው ለማድረግ÷ ለመጠበቅና ለማስፋፋት: ቃል ኪዳን የገባ "ክርስቲያን" ማለት ስለኾነ: ከላይ የተመለከተውን: በድርጅቱም ኾነ በብሔራዊው ደረጃ የሚታየውን የተዛባ አሠራር: ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ኹሉ: በብርቱ አስበውበት: ራሳቸውን: በንስሓ÷ ድርጊታቸውንም: በእውነተኛ ኢትዮጵያዊነት ማስተካከልና ማብቃት ይኖርባቸዋል::

## የእግዚአብሔር መንግሥት መገለጫዋ ሰውነት::

ኢትዮጵያውያን: በተከታታይነት የተፈጸሙትን: እኒህን ቅዱሳት ኪዳናት: ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው: ማለትም: ከአዳምና ሔዋን የፍጥረት ዘመን አንሥቶ: በዘመነ ሥጋዌ: እስከኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም መገለጥ ድረስ: ያልተቆጠበና ያልተገደበ÷ ወደር የሌለውንም መሥዋዕትነት በመክፈል: በሙሉ ጠብቀዋቸው ኖረዋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ: የኢትዮጵያ አካላዊትና አማናዊት መገለጫ ከኾነችው: ከድንግል ማርያም: በሰውነት በተወለደ ጊዜ: እነዚህ ቅዱሳት ኪዳናት: በእርሱ ሥጋዌ: ፍጹም የኾነውን: አካላዊና አማናዊ ግዝፈት መቀዳጀታቸው ታወቀ! በዚህም: ከእግዚአብሔር የተነገሩት የትንቢት ቃላት ኹሉ: የመጨረሻውን ብቅዓት አግኝተው መፈጸማቸውና እግዚአብሔር: ለፍጥረቱ ያዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅድ: ከተወጠነለት ግብ መድረሱ ተረጋገጠ::

ይህ የኢትዮጵያውያን ትውፊት: ከላይ እንደተወሳው: "ሕያው ነው" የተባለበት ዓቢይና ልዩ ምክንያት አለው:: ይኸውም: በቅዱሱ ኪዳን ውርስና ቅርስ ላይ የተመሠረተው: የኢትዮጵያውያን ትውፊት: ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ: ተጠብቆ የኖረው: እንዲያው በተለመደውና ተራ በኾነው: በግዑዙ ቍሳቍስ ላይ በሚቀረጸው ሰው-ሠራሽ ዘዴ ሳይኾን: በተለይ ለመለኮት ዘለዓለማዊ ሥራ: ሕያው መገለጫው በኾነው: በኢትዮጵያዊው ሰውነት በመኾኑ ነው::

አዎን! በመጨረሻው ዘመን: የአዲሱ ኪዳን መሥዋዕት በኾነው: በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም: ታድሶና ተጠናክሮ: ለዘለዓለማዊው ሕይወት የበቃው: ያ ኢትዮጵያዊ ሰውነት: ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ: እስከዚህ እስከዛሬው ጊዜ ድረስ ለቆየው: ከሰባት ሺህ ዓመታት በላይ ለኾነው ዕድሜ: የእነዚህ ሰባት ቅዱሳት ኪዳናት መለኮታዊ ማኅደር በመኾን አገልግሏል:: እንኳንስ ቀደም ብሎ: ባሁኑ ጊዜም ቢኾን: እግዚአብሔር: ከሰው ዘር ጋር ካደረጋቸው: ቃል ኪዳናት: ሕያው ምስክሩ: በእርግጥ: ኢትዮጵያዊው ብቻ ኾኖ ይገኛል:: ይህ እውነታ: በዐይነተኞቹ ኢትዮጵያውያን ሕይወት ላይ ገሃድ ኾኖ ዛሬም ስለሚታይ: አማናዊነቱን ለማስተባበል ከቶ አይቻልም::

እንዲህ እንደመኾኑና ማናቸውም እውነተኛ ክርስቲያን፡ ሊኾን እንደሚገባው ኹሉ፡ "ኢትዮጵያዊው ግለሰብ፡ የብሉዩንና የሐዲሱን ኪዳናት የያዙት፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ሥጋ ለብሰው፡ ሕያው የኾኑበት ሰብአዊ አካል ነው" ብለን አረጋግጠን እንናገራለን። ይህ፡ ለብፅዕና የሚያበቃ ጸጋ፥ ከረዥም ዘመናት በፊት፡ በነቢዩ ኤርምያስ ትንቢታዊ አንደበት የተነገረው፡ ከዚህ የሚከተለው፡ የእግዚአብሔር ቃል፡ ቀደም ብሎ፡ በበዓለ ሃምሣ ዕለት፡ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉት በሐዋርያትና ይኸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ወዲያው ተከታትሎ በወረደበት፡ በዚያ፡ "የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ" በተባለው፡ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ላይ ደርሶ፡ የመፈጸሙን ምሥጢር ያበሥርልናል።

ቃሉም እንዲህ ይላል፡- "*'እነሆ፥ ከእስራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል!' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ፡ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን፡ ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም! እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል አልኳቸው!' ይላል እግዚአብሔር። 'ከእነዚያ ወራት በኋላ፡ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና!' ይላል እግዚአብሔር፤ 'ሕጌን በልቡናቸው አኖራለሁ! በልባቸውም እጽፈዋለሁ! እኔም አምላክ እኾናቸዋለሁ! እነርሱም ሕዝብ ይኾኑኛል። እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን፥ እያንዳንዱም ወንድሙን፡ 'እግዚአብሔርን እወቅ!፡ ብሎ አያስተምርም፤ ከታናሹ ጀምሮ እስከታላቁ ድረስ፡ ኹሉ ያውቁኛልና!' ይላል እግዚአብሔር። 'በደላቸውን እምራቸዋለሁና! ኃጢአታቸውንም፡ ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና!'*" እነዚህን የትንቢት ቃላት፡ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትምህርቶቹ ውስጥ አውስቷቸዋል፤ ሐዋርያው[፴፮] ጳውሎስም፡ ወደዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ውስጥ ጠቅሷቸዋል።

በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ተመሥርታ የታነጸችው መለኮታዊት መንግሥቱ፡ በእንዴት ያለ ኹኔታ፥ በምን ጊዜና በየትኛው ቦታ፡ በገሃድ ገዝፋ እንደምትሠራ፡ ብሩህና ቀጥተኛ በኾኑት፡ በእነዚህ ሕያዋን ቃላቱ፡ እግዚአብሔር፡ ፍጹም ግልጽ አድርጎ አሳይቷል።

እግዚአብሔር፡ ለዚህች መንግሥቱ አመሠራረትና አቋቋም፥ አመራርና አካኼድ፡ እጅግ የተራቀቁትና ውስብስብ የኾኑት፡ የሰው ልጆች፡ ድርጅታዊና ማኅበራዊ፥ ትምህርታዊና ንዋያዊ ሥርዓቶችና ጥበቦች አላስፈለጉትም፤ አዎን! እነዚህ ኹሉ፡ ሰው፡ ራሱን በራሱ፡ በሙስና (በብልሹነት) እንዲደመስስ እስከማድረግ የሚያደርሱ፡ ሕፀፅን (ጉድለትን) እና ስሕተትን፥ ድክመትንና ስስትን የተመሉ ናቸውና፡ አላስፈለጉትም።

ዛሬ፡ በዚህ ቁሳዊ ዓለም፡ መልካሚቱን ኑሮ ለመኖር፥ ወደፊትም፡ ለሚመጇት ፍጽምት ዓለም ለመብቃት ይችሉ ዘንድ፡ የሰውን ልጆች፡ ወደእውነትና ወደሕይወት ልዕልና የምታደርሰው መንገዱ፡ የምትመራበትን ዘለዓለማዊ መርሐ ግብርና የምትሰጠውን ጠቃሚ አገልግሎት፡ በሥራ ላይ ለማዋል፡ እንደሰብአዊ መንግሥት፡ ሕዝባዊ መመሪያን ወይም የሕግ አዋጅን፥ ወይም የገንዘብ ወጪ ድልድልንና ርስት ጉልትን፥ ወይም የሠለጠነ የሰው ኃይልንና የትምህርት መሣሪያን፥ ወይም መሠረታዊ የልማት አውታርንና ባለብዙ ዘርፍ የጽሕፈት ቤት ተቋምን፥ ወይም፡ አስገዳጅ የጦር ኃይል ያለውን፡ የሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣንን አልፈለገም፡ እግዚአብሔር።

ኹሉን ማድረግ የማይሣነው: እርሱ: ኃያሉ እግዚአብሔር: የዘውድ መንግሥቱን: በምድር ላይ መሥርቶ ለማካኼድ ያስፈለገችው አንዲት ቅንጣት ነገር ብቻ ኾና ተገኘች! እርሷም: ህልውናዋና አምልኮዋ: በእውነትና በመንፈስ ላይ የተመሠረተ: *የዋህና ትሑት+ ታማኝና ተነሳሒ የኾነች ሰብአዊት ልቦና ናት::*

እግዚአብሔርም: ያችን ልቦና ለማግኘት: ከዘመነ ፍጥረት አንሥቶ: በአዳምና ሔዋን+ ከዚያም በልጅ ልጆቻቸው ሰውነት: ፍለጋውን ጀመረ፤ እነሆም: በተለይ ለቃል ኪዳኑና ለአገልግሎቱ በበቁት: በኖኅና ሚስቱ+ በመልከ ጼዴቅ+ በአብርሃምና ሣራ+ በካህኑ ዮቶርና ሚስቱ+ በሙሴና ሲጳራ+ በዳዊትና ቤትሳባ+ በሰሎሞንና ማክዳ ተያይዛ እየወረደችና እየተጠበቀች ኖራ: በመጨረሻ: በአማናዊዋ ሔዋን: በድንግል ማርያም ሰውነት ውስጥ: ለፍጹምነት በቅታ አገኛት! በእርሷም ማኅጸን: እግዚአብሔር ቃል: "አማናዊውና ዳግማዊው አዳም" ተብሎ: በኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋዌ አካል ተገለጸ! የዛሬው አዳም: ኢትዮጵያዊውና የዛሬዋ ሔዋን ኢትዮጵያዊቷም: ቅዱሱን ኪዳን: ከኢየሱስ ክርስቶስና ከድንግል ማርያም: በመንፈስ ቅዱስ ተረክበው: ይኸው: እስካሁን በባለአደራነት ጠብቀው ለማቆየት ችለዋል!

አዎን! እግዚአብሔር: በትስብእት (መለኮት በተዋሃደው የሰውነት) ደም ታድሶ በጸናው: በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት የምትተዳደረውን+ በልጁ: በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም እናታዊ ንግሥትነትም የምትመራውን: ዘለዓለማዊት የዘውድ መንግሥቱን: ህልውናዋ: በቀደሙት ተከታታይ የዘመነ ብሉይ ቃል ኪዳናት እየለመለመ በቀጠለው: በዚች: ሕያውት በኾነችው: ኢትዮጵያዊት ዓለት ልቦና ላይ መሠረተ::

እግዚአብሔር: ለሰው ዘር የሰጠውን+ በኢትዮጵያውያንም ዘንድ: እስከዛሬ ጸንቶና ተጠብቆ የኖረውን: ይህን: ወሰንና ወደር የሌለውን: የተትረፈረፈ ጸጋ: በመላው ዓለም የሚኖሩ እውነተኞች ክርስቲያኖች ጭምር የሚጋሩት እንጂ: የኢትዮጵያውያን ብቻ አለመኾኑ: እዚህ ላይ ሊታወቅ ይገባል::

\+ + +

# ኢትዮጵያ፡

አዎን! የዐምሐራው ኀብረተሰብ፡ ከአዳምና ሔዋን ተነሥቶ፥ በወንድሙ በቃየል የተገደለው፡ የልጃቸው የአቤል ምትክ በኾነው፡ በእሴት፥ ከዚያ፡ በኖኅና በልጆቹ፡ በሴም፥ በካምና በያፌት ነገዶች ውህደት በተገኘው በመልከ ጼዴቅ አማካይነት ሲወርድ ሲዋረድ የቀጠለው፡ የቅዱሱ ኪዳን ዘር እንደመኾኑ፡ የዚህ ኀብረተሰብ ጥንታውያን አባቶችና እናቶች፡ በሥጋ ለወለዷቸው፡ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች የመኾንን ክብር፡ በውርስ እንዲረከቡ በማድረግ፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም፡ ከፍጹምነት ለደረሰው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ሕዝብነት አብቅተዋቸዋል።

እስቲ ዛሬ፡ የትኛው ኢትዮጵያዊ ነው፡ ወይም፡ ከላይ በጥቂቱ በተወሱትና ከየራሳቸው ጠባብ ብሔረኝነት ጋር ተቆራኝተው በሚገኙት ጐሣዎች ውስጥ አባል ከኾነው ግለሰብ መካከል እንኳ ሳይቀር፡ የትኛው ነው፡ እንኳንስ፡ ከአንድ ነጠላ ጐሣ ይቅርና፡ "ከኹለት ወይም ከሦስት ጐሣዎች ብቻ የተወለድኩ ነኝ" በማለት፡ በሙሉ አፉ ደፍሮ ሊናገር የሚችል? ማንም ሊኖር ከቶ አይችልም። ምክንያቱም፡ ያ ኢትዮጵያዊ ወይም የጐሣ አባል፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ በወላጆቹ የትውልድ ግንድ በኩል፡ በጥቂቱ ወደኋላ ኼድ ብሎ፡ የአያቶቹን፥ የቅድማያቶቹንና የምዝላቶቹን የዘር ሓረግ ቢስብ፡ ራሱን፡ የኀብረብሔር ፍሬ፡ ማለት፡ እያሌ ጐሣዎች የተዋሃዱበት ቅይጥ ፍጡር ኾኖ ያገኘዋል። "ዐምሐራ" ወይም "ኢትዮጵያዊ"፡ ከሚያሰኙት ዓበይት ባሕርያት መካከል ደግሞ፡ ይህ፡ የኀብረ ብሔር ፍሬነት፡ አንዱ፡ ዓይነተኛው ባሕርይ መኾኑን፡ በትኵረት መመልከት ነው።

የዚህ እውነታ አማናዊነትና እርግጠኛነት፡ ባሁኑ ጊዜ፡ በኢትዮጵያ ምድር፥ እንዲሁም፡ በአገር ውስጥ በሚኖሩትና በውጭ አህጉር ተበትነው በሚገኙት ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ ሰፍኖ በሚታየው ኹኔታ፡ ጎልቶና ገዝፎ ይታያል። ይኸውም፡ ዓይነተኛው (እውነተኛው) የዐምሐራው ኀብረተሰብ፡ ኢትዮጵያ፡ በእግዚአብሔር መንግሥትነት ሥር ተዋህዳ የኖረች፡ የማትከፋፈል፡ አንዲት አካል መኾኗን በማመን፡ በጐሣ ወይም በዘር መለያየትን የሚቃወም በመኾኑ ነው።

እንዲያውም፡ ኢትዮጵያዊነት፡ ከዚህ የበለጠ፡ የመጠቀና የጠለቀ፥ የሰፋም ባሕርይ አለው፤ ይኸውም፡ ለኢትዮጵያ፥ እንዲሁም፡ ላለፉትና ለዛሬዎቹ፥ ለወደፊቶቹም ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ ተለይቶና ተወስኖ የተሰጠ፥ እየተሰጠ ያለና የሚሰጥም አለመኾኑ ነው፤ ነገር ግን፡ በዘመነ ሐዲስ ኪዳን፡ ሞክሼው (መሰሉ) እንደኾነው፡ እንደክርስቲያንነት ኹሉ፡ የሰው ዘር በመላ ተጠቃልሎና በመለኮታዊው መንግሥት ሥር ተዋህዶ፡ አንድ እንዲኾንበት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ለፍጥረተዓለሙ ደህንነትና መልካም ሕይወት፡ አዘጋጅቶ የዘረጋው ዘላለማዊ ዕቅድ ነው እንጂ። ይህም፡ በምድር ላይ ላለው፡ ለሰው ልጆች ችግር ኹሉ፡ የመጨረሻው መፍትሔ እንደሚኾን ይታመናል።

ከዚህ የተነሣ፡ ባንድ ወገን፡ "መላው ዐማራ" በሚል ስያሜ የተቋቋመው ድርጅት፡ በውስጡ፡ "ዐማራ" ከሚያሰኘው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ተዋህዶ ሃይማኖት ውጪ የኾኑትን ግለሰቦች ጭምር፡ በአባልነት አጠቃልሎ እንዲይዝ በማድረግ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ በአገር-አቀፍ ደረጃ፡ "የዐማራው ክልል" በሚል ዕቅድ፡ የተጀመረውን የመከፋፈል ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመሞከር፡ የሚፈጸመው ድርጊት፡ በየመልኩ ሊወገዝ ይገባዋል።